## ኢትዮጵያውያንን ከራሳቸው መጠበቅ

### በፕሮፌሰር መስፍን "አዳፍኔ" ላይ አንዳንድ ሐሳቦች

ዓለማየሁ ገብረማርያም (ፕ/ር)

በገፅ 7



### "በዓለም ታሪክም ያለመስዋዕትነት ወደ ዴሞክራሲ የተሸጋገረ አገር የለም"

አቶ ማሙሸት አማረ

በገፅ 6




# የቀለም ቀንድ

ቅጽ 3 ቁጥር 16 ጥቅምት 30 ቀን 2008ዓ.ም ዋጋው ብር 10.00





## የኢሕአዴግ ትጥቅ አስፈቺ ስትራቴጂ

4

## በደቡብ አፍሪካ እንደገና በተቀሰቀሰው ጥቃት ከስድስት በላይ ኢትዮጵያውያን ተገደሉ

በደቡብ አፍሪካ እንደገና ባገረሸው ጥቃት ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ ብዙ የውጭ ዜጎች መሞታቸውና ንብረታቸው መውደሙ ተገለጸ። ደርባን አካባቢ የሚገኙ የዓይን እማኞችን ጠቅሶ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ እንደዘገበው ‹‹የውጭ ዜጎች ይውጡልን›› በሚሉ ደቡብ አፍሪካውያን ጥቃት ባለፈው ሳምንት ብቻ ከስድስት በላይ ኢትዮጵያውያን ተገድለዋል። የተገደሉት ሁሉም ኢትዮጵያውያን በ20ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙና በንግድ ሥራ የተሰማሩ ሲሆኑ ግድያው የተፈጸመባቸው በየሥራ ገበታቸው ላይ እንዳሉ መሆኑም በዘገባው ተመልክቷል።

‹‹ሁኔታውን ለፖሊስ ሪፖርት ብናደርግም መልስ ሊሰጡን ፈቃደኞች አይደሉም፤ በአገራችን የፈለግነውን የማድረግ መብት አለን የሚሉት ደቡብ አፍሪካውያን በውጭ ዜጎች በተለይ በሌሎች አፍሪካውያን ላይ ጥቃታቸውን ቀጥለዋል›› በማለት የሚገልጹት ተገኔ አቦዬ የተባሉ በደርባን የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ፤ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ምንም ዓይነት እርዳታ እያደረገላቸው እንዳልሆነ አብራርተዋል። ደቡብ አፍሪካውያን ለደሃ የኅብረተሰባችን ክፍል የሚሆነውን የሥራ ዕድል ስደተኞች ተቆጣጥረውታል በሚል ሰበብ ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ለውጭ ሰዎች ያላቸው ጥላቻ እየተባባሰ መጥቶ ሰውን አቃጥሎና አሰቃይቶ ወደመግደል ተሸጋግሯል። ደቡብ አፍሪካውያን ያልሆኑ ጥቁር አፍሪካውያንን ዒላማ ያደረገው ይኸው ጥቃት ከዚህ ቀደም በልዩ ልዩ ከተሞች የሚኖሩ አፍሪካውያን ስደተኞችን ሕይወት መቅጠፉና ያፈሩትን ንብረት ማውደሙ አይዘነጋም።

ከሦስት ወራት በፊት ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ አያሌ አፍሪካውያን መጎዳታቸውን ተከትሎ ብዙ የአፍሪካ መሪዎች ቁጣቸውን በመግለጻቸው ፕ/ት ጃኮብ ዙማ ችግሩን በቁጥጥር ሥር እንደሚያውሉት ቃል የገቡ ቢሆንም አደጋው መልኩን እየቀያየረ ቀጥሏል። የኢትዮጵያ መንግሥት የሞቱንና የተገዱትን ወገኖች በሚመለከት ያለው ነገር የለም።

## "የኤርትራ ምሽት" ለስደተኞች ደራስያን



በገፅ 9

## "ኅብረተሰቡ ወተት ይጠቀምም፤ አይጠቀምም ለማለት አይቻልም"

የኢፌዴሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

በገፅ 3

## ርእሰ አንቀፅ

# ያልተማከለ ጭቆና

አገዛዙ የጭቆና ቀንበሩን በሕዝብ ላይ ጭኖ ለረዥም ጊዜ እንዲቀጥል ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ (ምናልባትም ዋነኛው)፣ ያልተማከለ አምባገነናዊ ሥርዓት መዘርጋቱ ነው። ያልተማከለ አስተዳደርና አምባገነንነት አብረው የሚሄዱ አይመስሉም። በቻይናና በኢትዮጵያ ግን በሚገባ ተዋሕዋል። የፖለቲካ ሳይንስ ምሁራን አምባገነኖች ከሚወድቁባቸው ምክንያቶች አንዱ ያለአቅማቸው በሁሉም ቤትና በሁሉም ጉዳይ ላይ ልግባ ማለታቸው ነው ይላሉ። ሁሉንም ልቆጣጠር ማለት ምንም ነገር አለመቆጣጠርን ያስከትላልና ውድቀትን ያፋጥናል። የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ መሪዎች ይህንን ችግር ጠንቅቀው ተረድተውታል። በብሔራዊ ደረጃ፣ በክልል ደረጃ፣ በአውራጃ ደረጃ ወዘተ. ጭቆናን ማከፋፈል አስፈልጓቸዋል። ኢሕአዴግ በዚህ ረገድ ከቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ የተማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ።

ኮሚኒስት ፓርቲው ከሊቀ-መንበር ማኦ በኋላ በተለይ በኢኮኖሚው መስክ ብዙ ለውጦችንና የማሻሻያ ርምጃዎችን መውሰዱ ለቻይና እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለማድረጉ ብዙ ተብሏል፤ ብዙ ተጽፏል። ፓርቲው ካደረጋቸው ለውጦች መካከል በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሰው ያልተማከለ አስተዳደር መዘርጋቱ ሲሆን ይኸው ያልተማከለ አስተዳደር የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲቀረፉ፣ በተለይ በኢኮኖሚው መስክ ብዙ እምርታዎች እንዲመጡ በር ከፍቷል። አገልግሎቶች በተፋጠነና ተደራሽ በሆነ መልኩ እንዲቀርቡ፣ ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉም ይነገራል።

በሌላ በኩል ያልተማከለ አስተዳደር መዘርጋቱ ኮሚኒስት ፓርቲው ይበልጥ ወደ ሕዝቡ እንዲወርድ፤ ይበልጥ ሕዝቡንና የየክልሉን ኤሊቶች እንዲቆጣጠር ከፍተኛ እገዛ አድርጎለታል። በየክልሉ የድርጅቱን ቅርንጫፎች የሚመሩ አባላት በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ደረጃ እንዲወከሉ ተደርጓል። ያልተማከለ አስተዳደሩ በኢኮኖሚው መስክ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት እንዲያቀርብ ሁኔታዎችን ሲያመቻች፤ በፖለቲካው መስክ ደግሞ የኮሚኒስት ፓርቲው እጅ ይበልጥ እንዲረዝም፤ ይበልጥ በየአከባቢውና በየዜጎች ቤት እንዲገባ ረድቶታል። በክልሎች የሚኖረው ኤሊት በኮሚኒስት ፓርቲው ላይ እንዳይነሳ፤ ከፓርቲው የተለየ አስተሳሰብ እንዳያራምድ ሰፊ የመቆጣጠሪያ መንገድ ከፍቷል።

ኢሕአዴግ በዚህ ረገድ ከቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ጠንካራ ትምህርትና ተመክሮ ቀስሟል። እንዲያውም ‹‹ከመምህሩ ደቀ-መዝሙሩ›› እንዲሉ፤ ከኮሚኒስት ፓርቲው ላቅ የሚልባቸው ደረጃዎች ሁሉ አሉ ለማለት ይቻላል። የዘመነ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያ ብሔረሰብ-ተከል በሆኑ ክልሎች የተዋቀረች አገር ናት። አራቱን ክልሎች የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች፣ የተቀሩትን ደግሞ ‹‹አጋር ድርጅቶች›› የሚባሉት ይቆጣጠሯቸዋል። በየትኛውም ክልል ከኢሕአዴግ የተለየ ፕሮግራም ያለው ድርጅት ሥልጣን ሊይዝ አይችልም፤ አልያዘምም። የአራቱ ክልሎች የተወሰኑ አመራሮች የኢሕአዴግ ሥራ አስፈጻሚ አባላትም ናቸው። የተወሰኑ የአጋር ድርጅቶች አመራሮችም በካቢኔ አባልነት ይሳተፋሉ። ብዙ፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ፕሮግራም ያላቸው ድርጅቶች በየክልሉ ተሰይመዋል። አንድ ድርጅት በሁሉም ጉዳይ ላይ እጁን ከሚያስገባ በሌሎች አማካኝነት ዓላማውን ቢያስፈጽም በጣም ተመራጭ ይሆናል። ሶማሌ ክልልን በሶሕዴፓ፣ ጋምቤላን በጋሕዴን ወዘተ. አማካኝነት መቆጣጠር ነገሩን ቀላልና ውጤታማ ያደርገዋል። ሁሉም ክልሎችን የሚመሩ ድርጅቶች እስከታች እስከጎጥ በተዘረጋው መዋቅራቸው የደርግን ጊዜ በሚያስንቅ መልኩ ሕዝቡን እያስጨነቁት ይገኛሉ። የስብሰባ ጋጋታ፣ የመዋጮ መዓት ሕዝቡን ከመጠን በላይ አስመርሮታል።

የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ያልተማከለ አስተዳደሩን ቢያንስ ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት ተጠቅሞበታል። ኢሕአዴግ በዚህ መሥፈርት ሲገመገም ቦዶ ነው። አሁንም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ በኋላ ቀር አሠራር የተተበተበ ነው። የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ የተባሉ ፕሮግራሞች ሁሉ ፉርሽ ሲሆኑ ነው የሚታየው። አንድ ሰሞን መንግሥት አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል እየሠራ ስለመሆኑ ባለሥልጣናቱም፣ መገናኛ ብዙኃንም እስኪሰለቸን ድረስ ይነግሩናል። ‹‹አንዳንድ የዚህ አካባቢ ነዋሪዎች በዚህ መሥሪያ ቤት አገልግሎት አሰጣጥ መደሰታቸውን ገልጹ›› እየተባለ ብዙ ይተረካል። ይሁን እንጅ በአገልግሎት አሰጣጣቸው ተሸለሙ የሚባሉት መሥሪያ ቤቶች ከነጭራሹ በቢሮክራሲያዊ አሠራር የታነቁ ሆነው ይገኛሉ። ከመቼውም ጊዜ በላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ በስርቆትና በዘረፋ እየተበከለ በመምጣቱ አሁን አሁን ያለ ጉቦ አገልግሎት ማግኘት የሚቻል አልሆነም። ኢንቨስተሮችና ሌሎች ተገልጋዮች ሁልጊዜ እንዳማረሩ ነው። በዚህ አካሄዳችን ከቀጠልን ናይጀሪያንም ሳናስንቅ አንቀርም።



## ትዝብት

በዕውቀቱ ስዩም

# የበዕውቀቱ ስዩም ሽሙጥ !

የአገር ፍቅር ቲያትር የግጥም ውድድር ማውጣቱን ሰማሁ። ግጥሙ በህዳሴ ግድብ ዙርያ -በተጀመረው ለውጥ ዙርያ - በኪራይ ሰብሳቢነት ዙርያ - በጥቃቅንና አነስተኛ ዙርያ - በትምህርት ጥራትና ሽፋን ዙርያ - እንዲሁም በሴቶች ተጠቃሚነት ዙርያ ማተኮር እንዳለበት ተገልጿል። እኔም በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ያተኮረች እልል ያለች ግጥም ልኪያለሁ። በውድድሩ አንደኛ እንድወጣ የምትፈልጉ በሞባይላችሁ ‹‹8700 A›› በመጫን አጋርነታችሁን እንድታሳዩ እማጸናለሁ።

የወሎ ከተማ፤ ትባላለች ደሴ፣
እንዴምን ከርመሃል፤ ታላቁ ህዳሴ፣
የቆንጆ መፍለቂያ፤ ትባላለች ደሴ፣
እንደ ሰርኬስ ባቡር፤ ተገትሮ
እንዳይቀር ታላቁ ህዳሴ።
ቡልኬት ማዋጣት፤ አለብን እላለሁ፣
ስሜን ለማታውቁት፤ በውቀቱ
እባላለሁ።

የተጀመረው ለውጥ፤ እጅግ አሳሳቢ፣
የዚህን ወር ማረኝ፤ ጋሽ ኪራይ
ሰብሳቢ።

በጥቃቅንና፤ አነስተኛ ኑሮ፣
እቅመደመዳለሁ፤ ጉዴ ነው ዘንድሮ።

የትምህርቱ ጥራት፤ ቢሆንም የሾቀ፣
ሽፋኑ ወርቅ ነው፤ እጅግ የደመቀ፣
የግጥሙ ፀሐፊ አገሩን ናፈቀ ።

ሴቶች ተጠቃሚ፤ ወንዱም ተጠቃሚ፣
በዚህ ከቀጠለ፤ እጅግ ያሳስባል፣
የኮንዶም አቅርቦት፤ ሊስፋፋ ይገባል።
(በፌስቡክ ገጹ ያሰፈረው)

በዲኦንሔር ፐብሊሺንግ ሚዲያ እና ኮምኒኬሽን ኃላ.የተ.የግ. ማኅበር እየተዘጋጀ የሚቀርብ ሳምንታዊ ጋዜጣ

**ሥራ አስኪያጅ**
አበበ ውቤ

**ዋና አዘጋጅ**
ሙሉቀን ተስፋው
0910159783
mulukentesfaw@gmail.com
የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁጥር 09/297


**ሪፖርተር**
ትሑት ጥላሁን

**አምደኞች**
መስከረም አበራ
ቴዎድሮስ ኃይለማርያም (ዶ/ር)
ሩት አማኑኤል
መብራቱ በላቸው
በሪሁን አዳነ

**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
ቂርቆስ ክ/ከተማ ወረዳ 08
ቤ/ቁጥር 471
ስልክ፡ 0910159783
0919396240

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ስልክ፤ 0911 18 09 33

**አታሚ**
ናታን ማተሚያ ቤት
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 1062



# ዜናዎች

## “ኅብረተሰቡ ወተት ይጠቀምም፤ አይጠቀምም ለማለት አይቻልም”

### የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር

በአዲስ አበባ የከብት ወተትና የወተት ተዋጽኦዎች ተበክለዋል በሚል የሚናፈሰው መረጃ የተሟላ ጥናትን መሰረተ ያደረገ አይደለም ያለው የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ሆኖም ኅብረተሰቡ ወተት ይጠቀም ወይንም አይጠቀም ለማለት እንደማይቻል ገልጿል። በአዲስ አበባ ዙሪያ የሚገኙ የወተትና የወተት ተዋጽኦ ምርቶች በሻጋታ ምክንያት የሚፈጠር የአልፋ ቶክሲን መጠናቸው ከፍ ብሏል፤ ይህም ከዓለማቀፍ መስፈርት በላይ ነው በሚል አንተርናሽናል ላይቭ ስቶክ ሪሰርች ኢንስቲትዩት ያወጣው ሪፖርት ሳይንሳዊ መመዘኛዎችን አካቶ የተሠራ አለመሆኑን ሚኒስቴሩ ጠቁሟል። ተቋሙ ያሰራጨው መረጃ ወቅቱ የሚጠይቀውን መሳሪያዎች ተጠቅሞ ያልተጠናና ሁሉንም ስፍራዎች ወካይ በሆነ መንገድ ያካተተ ባለመሆኑ ተጨባጭነት ይጎለዋል ነው ያለው።

መረጃው ከወጣበት ቀን ጀምሮ በርካቶችን የተሳሳተ አስተሳሰብ ውስጥ እየከተተ በመምጣቱም ከጤና ጥበቃ ሚኒስቴር፣ ከእራሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ ከዓሣና እንስሳት ሀብት ሚኒስቴር እንዲሁም ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተውጣጣ ግብረ ኃይል አቋቁሞ ጥናት ማድረግ እንደጀመረ ተገልጿል። ጥናቱ በዋናነት ከከብቶቹ ርቢ አንስቶ የሚጠቀሙትን መኖ የሚዳስስ፤ የምርት ሂደትና ድህረ ምርትን የሚያካትት ነው። በኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሚመራው ቡድን የሚያካሂደው ጥናትም የወተት ናሙና ሰብስቦ ላብራቶሪ ገብቷል።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ አቶ አሕመድ ኢማኑ በሰጡት መግለጫው፣ አልፋ ቶክሲን የሚባለው ኬሚካል ገና ከእርሻ አንስቶ የሚከሰት ነው እንጂ ድንገት በአንድ ቀን ወተትና የወተት ተዋጽኦን የሚበክል አይደለም ብለዋል። ሆኖም መንግሥት ጉዳዩን ቸል አላለውም ነው ያሉት አቶ አሕመድ። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ጉዳዩን አስመልክቶ ሁሉንም አካባቢዎች ባካተተ መልኩ በዘመናዊ መሣሪያዎች እያካሄደው ያለው ጥናት ሙሉ ውጤት በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ይፋ እስኪደረግም ኅብረተሰቡ ባልተረጋገጠ መረጃ ከመረበሽ እንዲቆጠብ አሳስቧል። ይሁን እንጂ ጥናቱ ተጠናቆ ትክክለኛ ውጤት እስካልተገኘ ድረስ በመላምት ብቻ ኅብረተሰቡ ወተት ይጠቀም፤ አይጠቀም ማለት እንደማይቻል ተናግረዋል።

## “የፍትሕ ሥርዓቱ የአገዛዙ መግዢያ፣ ፍርድ ቤትም በተራ ካድሬ የሚታዘዝ ሆኗል”

### ሰማያዊ ፓርቲ

ሰማያዊ ፓርቲ ጥቅምት 24 ቀን 2008 ዓ.ም. በሰጠው መግለጫ ከነካባው የተቀበረውን የፍትሕ ሥርዓት ነጻ ለማውጣት ትግላችን ማጠናከር አለብን ሲል ገለጸ። ፓርቲው በመግለጫው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ማናቸውም ሕጎች፣ ሕገ መንግሥቱን ጨምሮ ለአገዛዙ ማጥመቂያና መግዣ መሣሪያ ከመሆን የዘለለ የዜጎችን መብት እያስከበሩ አይደለም ብሏል። የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር አቶ ይልቃል ጌትነትና ምክትል ሊቀመንበሩ አቶ ነገሠ ተፋረደኝ ከጋዜጠኞች ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ‹‹ሕገ መንግሥቱንም ሆነ ሌሎች የፍትሕ ማሕቀፎችን በመናድ መንግሥት ግንባር ቀደም ተዋናኝ ሆኗል›› ብለዋል።

የፍትሕ ሥርዓቱ ለአገዛዙ መግዢያ፣ ፍርድ ቤቶችም በተራ ካድሬዎች የሚታዘዙ መሆናቸውን የሚያትተው የሰማያዊ መግለጫ ፍርድ ቤት ነጻ ብሎ የለቀቃቸውን ግለሰቦች ያለ ካድሬዎች መልካም ፈቃድ ከማረሚያ ቤት አሊያም ከማዕከላዊ መውጣት እንዳልቻሉ ናሙና በማንሳት ይዘረዝራል። የሰማያዊ ምክትል አፈ-ጉባኤ አቶ የሸዋስ አሰፋና ከእሱ ጋር በአንድ መዝገብ የተከሰሱ ፖለቲከኞችና ሌሎች ግለሰቦች ቤታቸው ተፈትሾ ምንም ነገር ሳይገኝ በማእከላዊና በሌሎች የምርመራ ቦታዎች ሁሉ ሰብአዊ መብታቸው ተጥሷል፤ መብታቸው መጣሱን ለፍርድ ቤቱ በማስረዳታቸው ብቻ ‹‹ችሎት ደፋራችሁ›› በሚል ለተጨማሪ ቅጣት ተዳርገዋል።

በባህር ዳር የፓርቲው አመራር በ15 ሺህ ብር ዋስ እንዲወጣ ፍርድ ቤት ቢወስንም ካድሬዎቹ ባለመፍቀዳቸው ብቻ አሁን በእስር እንደሚገኙ ተገልጧል። በአቶ አለነ ማሕጠንቱ ላይም የደረሰው ተመሳሳይ ነው ተብሏል። በጎንደርና በሸዋሮቢት በርካታ ዜጎች ለወራት ታጉረው ከቆዩ በኋላ ወደ ማእከላዊ የተዛወሩ ቢሆን ቤተሰብ እንዳይጠይቃቸው መደረጉ በመግለጫው ተካቷል። እንደ መግለጫው በአርባ ምንጭም በርካታ የፓርቲው አባላት እንደታሰሩ በቅርቡም ወደ ማእከላዊ ተዛውረዋል። በእነ አንዷለም አራጌ፣ እስክንድር ነጋ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ አብረሃ ደስታ፣ ሀብታሙ አያሌውና ዳንኤል ሽበሽ እንዲሁም በሌሎች ፓለቲከኞችና የህሊና እስረኞች ላይ የሚደርሰው የመብት ረገጣ ሕግ ከነካባዋ ለመቀበሯ ምስክር ነው ተብሏል። ሰማያው ፓርቲ ‹‹ትግላችንን ከዳር ለማድረስ የሚመለከታቸው የፖለቲካ ኃይሎች፣ የኢትዮጵያ ሕዝብና ዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ከጎናችን እንዲቆም ጥሪያችን እናስተላልፋል›› በማለት መግለጫውን አጠቃሏ።

## በረኀብ የተጎዱ ዜጎች ቀያቸውን ለቀው እየተሰደዱ ነው

በተከሰተው ድርቅ ምክንያት በረኀብ በተጠቁ ዜጎች ሕይወታቸውን ለማቆየት ቀያቸውን ለቀው በመሰደድ ላይ ናቸው። ወደ አዲስ አበባና ሌሎች አካባቢዎች በመግባት ላይ የሚገኙት በርካታ ተጎጂ ኢትዮጵያውያን በመንግሥት በኩል በቂና አፋጣኝ እርዳታ እያደረገላቸው እንዳልሆነና ሕይወታቸውን ከአደጋ ለመታደግ ቀያቸውን ለቀው ለመውጣት እንደተገደዱ አብራርተዋል። መንግሥት አፋጣኝ እርምጃ ካልወሰደ በስተቀር በጥቂት ጊዜያት ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ወደከተሞች መጉረፉን እንደሚቀጥልም ጠቁመዋል።

መንግሥት በኤልኒኖ ሳቢያ በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ብዙ ዜጎች አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልጋቸው ቢያምንም ችግሩ ከመንግሥት አቅም በላይ እንዳልሆኑ ሲገልጽ መቆየቱ አይዘነጋም። ይሁን እንጂ የችግሩ ተጎጂዎችና ዓለም ዐቀፍ ተቋማት የችግሩ ግዝፈትና አሳሳቢነት መንግሥት ከሚለው በእጂጉ እንደሚበልጥና አፋጣኝ የሆነ እርዳታ ካልተደረገ ችግሩ እየከፋ መሄዱ እንደማይቀር በማሳሰብ ላይ ይገኛሉ።

## ዘግናኝ ግድያ በሽሮ ሜዳ

ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም. አንድ ግለሰብ አዲስ አበባ ሽሮ ሜዳ በሚባለው አካባቢ በአሜሪካ ኢምባሲ ፊት ለፊት ሁለት ሰዎችን በቢለዋ አርዶና በእሳት አቃጥሎ መግደሉን የሟች ቤተሰቦች ለቀለም ቀንድ ጋዜጣ ገልጸዋል። የዝግጅት ክፍላችን ይህን ዘግናኝ አደጋ በሐዘን ቤት ተገኝቶ ለማጣራት የሞከረ ሲሆን የሟች ተማሪ አቢሲንያ ፋንታሁን አባት አቶ ፋንታሁን ብርሃኑ በስልክ ተደጋጋሚ ማስፈራራትና ዛቻ ይደርሳቸው እንደነበር ገልጸዋል። ‹‹የመግባባትና አንድነት ሰላም ማኅበር›› መሥራችና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት አቶ ፋንታሁን በተለያየ ጊዜ ለእስር መዳረጋቸውም ታውቋል። የአዲስ ዓመት ዋዜማን ምክንያት በማድረግ ከእስር የተፈቱት አቶ ብርሃኑ ተከታታይና የማያቋርጥ በደህንነቶች የማስፈራራት ዛቻ እንደደረሰባቸው፣ ማንነታቸው ያልታወቀ ሰዎች በስልክ አፍነን እንገልሃልን እንደሚሏቸው ገልጸው፣ ነገር ግን ግድያው ከዚህ ዛቻ ጋር የተያያዘ መሆን አለመሆኑ እርግጠኛ አለመሆናቸውን ጨምረው አብራርተዋል።

በግድያ ወንጀል የተጠረጠረው አቶ ኽይሩ ጀማል የታላቅ ልጃቸው ጓደኛ ሲሆን በአንድ ቤትም መኖር ጀምረው ነበር። ‹‹ቀደም ባሉት ጊዜያት አንዳንድ ሰነዶች ከቤቴ ሲጠፉ ተጠራጥሬው ነበር። በልጄ ፍላጎት ጣልቃ ሳልገባ ዶክመንቶቼን መኝታ ቤት እየቆለፍኩ መጠንቀቅ ጀመርኩ። በእኔ እንጅ በልጄ ላይ ፈጽሞ ይህ ነገር ይፈጠራል ብየ አስቤ አላውቅም›› ይላሉ አቶ ፋንታሁን። ተማሪ አቢሲንያ የ7ኛ ክፍል ተማሪ ስትሆን በጠዋት ፈረቃ ትምህርቷን ጨረሳ 7፡00 ሰዓት ቤቷ ተመልሳለች። አቶ ፋንታሁን ሁልጊዜ ከቤታቸው ምሳ የመብላት ልምድ ቢኖራቸውም በጊዜው አልነበሩም። ባለቤታቸውም ሥራ ቦታ ነበሩ። ግለሰቡ መጀመሪያ ማንን ለመግደል አስቦ እንደነበር የታወቀ ነገር ባይኖርም ሁለቱን ሰዎችን ከገደለና ሰውነታቸውን ካቃጠለ በኋላ ሙዚቃ ከፍ ባለድምጽ ከፍቶ በጀርባ በኩል በጎረቤት በር ለመሄድ ሲሞክር ጎረቤቶቻቸው የልጁን ያልተለመደ ገጽታ አይተው ይይዙታል። ልጁን ይዘውት ሲመጡ ቤቱ ውስጥ ያለው ቃጠሎ ጭስ በውጭ በኩል ይታይ ነበር። በሩ ሲከፈት ሁለት ግለሰቦች ወዳድቀዋል። ተማሪ አቢሲንያ አንገቷ በቢለዋ የታረደ ሲሆን የአቶ ፋንታሁን ጎረቤትና የሰላምና የአንድነት ማኅበሩ ሒሳብ ሹም እንዲሁም የቀድሞ የሰማያዊ ፓርቲ የብሔራዊ ምክር ቤት አባል የነበሩት የ60 ዓመት አዛውንት አቶ አበራ ኃይለ ማርያም ፊታቸው ተቃጥሎ ሞተው ተገኝተዋል። አቶ አበራ ከቤታቸው የወጡት ሽንት ቤት ደርሰው ለመመለስ ቢሆንም እንደወጡ አልተመለሱም። ተጠርጣሪው ሁለቱንም ግለሰቦች ከገደለ በኋላ ብርድልብስና አንሶላ በላያቸው ላይ በማድረግ አቃጥሏቸዋል። ግለሰቡ በአሁኑ ወቅት በፖሊስ ቁጥጥር ሥር እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።

## <<በሶማሌ ክልል በቀላፎና ሙስታሂል ወረዳዎች የብሔረሰብ ዕውቅና ጥያቄ በማንሳታቸው ከ65 በላይ ሰዎች በአሰቃቂ ሁኔታ በጅምላ ተገድለዋል፤ ከ153 በላይ ቆስለዋል>>

### ሰመጉ

የሰብአዊ መብቶች ጉባኤ (ሰመጉ) ጥቅምት 23 ቀን 2008 ዓ.ም. ባወጣው 139ኛ ልዩ መግለጫው በሶማሌ ክልል በቀላፎና ሙስታሂል ወረዳዎች የብሔረሰብ የዕውቅ ጥያቄ ያነሱ የሬርባሬና የዱቤ ጎሳ አባላት በክልሉ ልዩ ኃይል በጅምላ የተገደሉ የ65 ሰዎችና በጥይት ቆስለው ለአካል ጉዳት እንደተዳረጉ ገልጾ የ115 ሰዎችን በስም ዝርዝር ይፋ አድርጓል። ሰመጉ በልዩ መግለጫው እንዳመለከተው በክልሉ የሚኖሩ የሬርባሬና የዱቤ ጎሳዎች ከ1990 ዓ.ም. ጀምሮ የዕውቅና ጥያቄ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ሲያቀርቡ ቆይተዋል። ‹‹ባሕላችን፣ ቋንቋችንና የመኖሪያ አካባቢያችን መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ ከሶማሌ ብሔረሰብ የተለየ በመሆኑ ልዩ ዞን እንዲሰጠን ጠይቀናል። ቀላፎ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና በደርግ ዘመን አውራጃ ነበር፤ በዚህ ምክንያት ታሪኩንና ባሕሉን መሠረት በማድረግ በዞን ደረጃ እንዲደራጅ እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ድረስ አመልክተናል›› በማለት እንደገለጹ ሰመጉ በመግለጫው አብራርቷል።

ሰመጉ የአካባቢውን ሽማግሌዎችን ዋቢ አድርጎ ባዘጋጀው መግለጫው በቀላፎ፣ ሙስታሂልና ፌርፌር ወረዳዎች ውስጥ ከሦስት መቶ ሺህ (300,000) የማያንሱ የሬርባሬ ጎሳ አባላት ሲኖሩ ከአምሳ ሺህ (50,000) በላይ የሚሆኑ የዱቤ ጎሳ አባላት በምሥራቅ አሚ እና በምዕራብ አሚ ወረዳዎች ይኖራሉ። እንደ ሽማግሌዎቹ ገለጻ በቀላፎ ከዐሥር ዓመት በፊት በተከናወነው የሕዝብና ቤት ቆጠራ የሬርባሬ ጎሳ አባላት 121,000 (አንድ መቶ ሃያ አንድ ሺህ) የነበረ ሲሆን፣ የኦጋዴን ጎሳ አባላት ቁጥር ደግሞ 4000 (አራት ሺህ) ነበር። በጠቅላላው በወረዳው 125,000 (አንድ መቶ ሃያ አምስት ሺህ) ሕዝብ ይኖራል። ይሁን እንጂ የሬርባሬ ጎሳ አባላት ቋንቋቸውና ባሕላቸው ከኦጋዴን ጎሳ የተለየ ሆኖ ሳለ ወረዳውን የሚያስተዳድሩትና በመንግሥት ሠራተኛነትም ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት የኦጋዴን ጎሳ አባላት በመሆናቸው ቅሬታው ተፈጥሯል። የሬርባሬና የዱቤ ጎሳዎች ሽማግሌዎች “የቀላፎ ወረዳ የቀድሞውን የአውራጃ ደረጃ በሚመጥን መልኩ ዞን እንዲሆን፣ እንደ ሌሎቹ ብሔረሰቦች በቋንቋችንና በባሕላችን የመጠቀም መብታችንና የማንነት ጥያቄያችን ተከብሮልን ራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ መብታችን እንዲጠበቅልን የሚል ጥያቄ አቅርበው ነበር። ይህን ጥያቄ ለምን አነሳችሁ በማለት የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ልዩ ፖሊስ ኃይል ታኅሣሥ 1 እና 2 ቀን 2006 ዓ.ም በፈጸመው አሰቃቂ የጅምላ ግድያ ከ65 ሰዎች በላይ የተገደሉ ሲሆን ከ153 በላይ ቆስለዋል። የሰመጉ ባለሙያዎች ድርጊቱ በተፈጸመባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት ጥቃቱ የተፈጸመባቸውን ዜጎችና ቤተሰቦቻቸውን በማነጋገር ድርጊቱ መፈጸሙን ለማረጋገጥ እንደቻለ በልዩ መግለጫው ላይ ተመልክቷል።

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሬርባሬ ጎሳ ተወላጆች ላይ ግድያና ማቁሰል ከመፈጸሙ በተጨማሪ ግምቱ 15 ሚሊዮን ብር የሚገመት እህል ከአውድማና ከማሳ ላይ ተቃጥሏል። የ150 አባውራዎች መኖሪያ ቤቶች ተቃጥለዋል። ይህንን ችግር ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት፣ ለኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ለአገር መከላከያ ሚኒስቴር፣ ለፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ለሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በተደጋጋሚ ማመልከታቸውን በመስክ ሥራ ላይ ለተገኙ የሰመጉ ባለሙያዎች የተጎጂዎች ተወካዮች በምሬት ገልጸዋል።

# የኢሕአዴግ ትጥቅ አስፈቺ ስትራቴጂ

በቅርቡ በአቶ በረከት ስምኦን የሚመራው የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከልና የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ኃይል ሚኒስቴር በጋራ ያጠኑት ነው በተባለለት የመልካም አስተዳደር ችግርን በሚመለከተው ጥናት ላይ አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ከድርጅቱ ከፍተኛ አመራሮች ጋር ያደረጉትን ውይይት ተከትሎ የተለያዩ አስተያየቶች እየተሰጡ ነው። አንዳንዶች ኢሕአዴግ ከጊዜ ወደጊዜ ራሱን ለማረም ቁርጠኝነት እያሳየ መምጣቱን ሲገልጹ ሌሎች የአሁኑ የድርጅቱ አካሄድ የተለመደ፣ ከዘመቻ የዘለለ ምንም ጠብ የሚል ለውጥ ሊያመጣ የማይችል ማደናገሪያና ተራ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ነው ይላሉ። ሪፖርተር ጋዜጣ (ቅጽ 21 ቁጥር 1619) ‹‹ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወሳኝነታቸውን ያሳዩበት መድረክ›› ሲል ያሞካሸው ይኸው መድረክ እንዴትና በምን ምክንያት የተለየ ሆኖ ሊቆጠር እንደቻለ ጨርሶ ግልጽ አይደለም።

## የተለመደው የ‹‹በስብሰናል›› መዝሙር

መቼም ኢሕአዴግ የዜጎችን ጩኸት መቀማት ይችልበታል። የተለመደው የጩኸት የመቀማት ስትራቴጂ፣ ሕዝቡ የሚማረርባቸውንና የተቃዋሚው ኃይል ዋና ዋና መከራከሪያ የሆኑ ጉዳዮችን በመቀማትና የራሱ በማድረግ ጥያቄውን ባይፈታውም ‹‹ኒውትራላይዝ›› ማድረግን የሚመለከት ነው። ጥያቄው የእኛም ጥያቄ ነው፤ ሕዝቡ ተማሮብናል፤ እንደ ድርጅት በስብሰናል፤ በብሔርና በልዩ ልዩ ኔትዎርኮች መተሳሰር አለ ወዘተ. ይባላል። የተወሰኑ ካደሬዎችና ባለሀብቶች ሰለባ ይሆናል። መንግሥት የሕዝቡን እሮሮ እየሰማና ቁርጠኛና ተግባራዊ እርምጃ እየወሰደ ነው፤ ሕዝቡም በትግሉ ከመንግሥት ጎን ተሰልፎ የመሪነቱን ሚና እየተጫወተ ነው ይባላል። ሚዲያውም እንደተለመደው ስለመንግሥት ‹‹ቁርጠኝነት›› እያጋነነ ይዘግባል። ዘመቻው ይቀጥላል። የተለመደው አካሄድ በአጭሩ ይህን የሚመስል ነው።

ሁሉም እንደሚያውቀው ዜጎች በመልካም አስተዳደር ችግር ታንቀው መከራቸውን ማየት የጀመሩት አሁን አይደለም፤ ድሮ ነው። በየመሥሪያ ቤቱ ከስብሰባና ከድርጅት ተግባር በስተቀር ሌላ ሥራ እንደማይሠራ፣ ሲቪል ሰርቫንቱ ደሞዙ እጅግ አነስተኛ መሆኑ ሳያንስ በስብሰባና ግምገማ አበሳውን እያየ በመሰላቸቱ ምክንያት ሕዝብ የሚያረካ አገልግሎት መስጠት እንዳልቻለ፣ በየመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ተብለው የሚመደቡት ብቃት የሌላቸው ታማኝ ካድሬዎች በብሔረሰብና በልዩ ልዩ ኔትዎርኮች ተደራጅተው አድሏዊ የሆነ የሥራ ቅጥር እንደሚፈጽሙ፣ ሠራተኛውን በማናለብኝነት እንደሚያጎሳቁሉ፣ ኢ-ፍትሃዊና ዘረኛ በሆነ መልኩ የዜጎችን ቤት እንደሚያፈርሱ፣ የራሳቸውን ብሔረሰብ አባላት በልዩ ልዩ መንገዶች እንደሚጠቅሙ፣ ሙስናና ስርቆት ከታች እስከላይ ሥር እንደሰደደ ወዘተ. ወዘተ. ብዙ ሲባል ከርሟል። ኢ-ፍትሃዊነት መንገሡም በብሔረሰብ መተሳሰሩም፣ የመሬት ዘረፋውም ሁሉም እንግዳ ነገር አይደለም። ይህን ሁሉ ወንጀል የሚሠሩት የራሱ የገዥው ኃይል አባላትና አመራሮች በመሆናቸው አገዛዙም የችግሩን ሁኔታ ግጥም አድርጎ ያውቃል።

ኢሕአዴግ የዜጎችን ጩኸት መቀማት ልማዱ ነውና፣ አሁንም እንደተለመደው ሞቻለሁ፤ በስብሻለሁ፤ የብሔር ኔትዎርኩ ሥር ሰዷል፤ ሕዝቡ በኢሕአዴግና በመንግሥት ላይ ተማሯል፤ የመሬት ዘረፋው (እነሱ ወረራ ይሉታል) ጣሪያ ነክቷል፤ በዚህ ሁኔታ ከቀጠልን እንበላለን ወዘተ. እያለን ነው። ድርጅቱ በራሱ ላይ የዚህ ዓይነት ‹‹ምህረት የለሽ ክስ›› ሲያቀርብ ይህ የመጀመሪያው አይደለም። ለአብነት ያህል እነ አቶ ገብሩ አሥራትን ከሕወሓት ካስወገደው ድርጅታዊ ክፍፍል በኋላ ኢሕአዴግ በአቶ መለስ ቋንቋ መበስበሱን ገልጾ ተሃድሶ የሚል ራስን የ‹‹ማጽዳና የማደስ›› ስትራቴጂ ተግባራዊ እንዳደረገ አይዘነጋም።

በእርግጥም ደግሞ በዚያ ተሃድሶ በተባለው የማጽዳት ዘመቻ የነአቶ መለስን አቋም ይቃወማሉ የታባሉ የድርጅት አባላትና አመራሮች ከታች እስከ ላይ ድረስ ተመንጥረዋል። ተሃድሶው ጠላትና ወዳጅን በግልጽ ለመለየት፣ ማን ከማን ጋር እንደቆመ ለመረዳትና ለመመንጠጠር ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ዘመቻውም ሁሉም ‹‹መለስ ማረኝ!›› እስኪልና አቶ መለስ ብቸኛው አይደፈሬ መሪ ሆነው መውጣት እስኪችሉ ድረስ ቀጥሏል። ይሁንና ተሃድሶ የተባለው ዘመቻ እነአቶ መለስን እንጂ ሕዝቡን በየትኛውም መንገድ ተጠቃሚ እንዳላደረገ ደግሞ በጣም ግልጽ ነው። ባለፉት አሥር ዓመታት የተመዘገበው ባለሁለት ዲጂት እድገት የዚያ ተሃድሶ የተባለው ዘመቻ ውጤት መሆኑን በተደጋጋሚ ብንሰማም ሕዝቡ ያገኘው አንዳችም ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው። ብዙሃኑ ሕዝብ አሁንም ራሱን መመገብ አልቻለም። ተፈጥሯል የተባለው ሚሊየነር አርሶ አደርም የውኃ ሽታ ሆኗል።

ይኸው የበስብሰናል መዝሙር ኢሕአዴግ በምርጫ 1997 ዓ.ም. አስደንጋጭና ያልታሰበ ሽንፈት ከደረሰበት በኋላም ቀጥሎ ነበር። አቶ መለስ በምርጫው ማግስት የራስ ምታት የሆኑባቸውን የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎች እስር ቤት ከወረወሩ በኋላ ከአማራ ክልል እስከ ጉራጌና ሃድያ ዞኖች ኢሕአዴግን አልመረጡም ባሏቸው አካባቢዎች ሁሉ እየተዘዋወሩ ‹‹የሚገባንን ያህል መሥራት ባለመቻላችን አዝናችሁብናል፤ ለዚህ ነው በምርጫ የቀጣችሁን፤ ተገቢ ተግሳጽ ነው፤ እናስተካክላለን›› ወዘተ. እያሉ ስለድርጅታቸው ውድቀት በሰፊው ሲናገሩ መክረማቸው አይዘነጋም። አቶ መለስ በተዘዋወሩባቸው አካባቢዎች ሁሉ አንዴ እያስተዛዘኑ አንዴ ደግሞ እያስፈራሩ፣ የዩኒቨርሲቲና የሆስፒታል የመሠረት ድንጋይ እያስቀመጡና ጋቢ ‹‹እየተሸለሙ›› ከፍተኛ የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ሲሠሩ ከርመዋል። ለአምስት ዓመታት የሕዝብ ግንኙነት ሥራ ሲሠሩ ቆይተው ድርጅታቸው በምርጫ 2002 ዓ.ም. ከአንድ የፓርላማ መቀመጫ በስተቀር ሁሉንም ጠራርጎ ሲወስድ አቶ መለስ ከማፈር ይልቅ ውጤቱ የሥራቸው ውጤት እንደሆነና እንደሚገባቸው መግለጻቸውን እናስታውሳለን።

የፖሊሲ ጥናትና ምርምር ማዕከል አጠናው የተባለው ጥናትና ጥናቱን ተከትሉ የተደረገው ውይይትም ከዚህ ቀደም ከነበሩት የኢሕአዴግ አካሄዶች ጋር በእጅጉ የሚመሳሰል ነው። የተለየ አዲስ ነገር አልታየበትም። አሁንም እንደትናንቱ እየተዘመረ ያለው ያው የተለመደው መዝሙር ነው። ‹‹አረንቋ ውስጥ ነን፤ የብሔር ኔትዎርክ ሥር ሰዷል፤ ሙስና ጣሪያ ነክቷል፤ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት አልቻልንም ወዘተ.›› እየተባለ ነው። አንዳንዶች መንግሥት የጥናቱን ውጤት መሠረት አድርጎ ጠንከር ያለ እርምጃ ሊወስድ እንደሚችል በመግለጽ ላይ ቢሆኑም ካለፈው ተመክሮ በሚገባ መገንዘብ እንደሚቻለው አገዛዙ እንደተለመደው የተወሰኑ ሰዎችን የእስር ሰለባ ከማድረግ የዘለለ ይኼ ነው የሚባል መሠረታዊ እርምጃ ሊወስድ አይችልም። አምስት ዓመት እየቆጠሩ የተወሰኑ ‹‹ትናንሽ አሳዎች››ን በማሳደድና በማሰር አረንቋ ውስጥ የገባውን የመልካም አስተዳደር ችግር መፍታት ደግሞ ፈጽሞ የሚታሰብ አይደለም።

በአገራችን የዴሞክራሲ ሽታ አለመኖሩን በሚገባ ከሚያረጋግጡ ነገሮች ውስጥ ይኸው የ‹‹በስብሰናል›› መዝሙር ተጠቃሽ ነው። በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ሕዝቡ የጣለበትን ኃላፊነት መወጣት ያልቻለ አመራርና ድርጅት ኃላፊነቱን እንዲያስረክብ ይገደዳል። በስብሻለሁ እያሉ አገር መምራት ብሎ ነገር የሚታሰብ አይደለም። አገዛዝ በአንጻሩ የተጽዕኖ ሥርዓት አይደለምና የሕዝብ አስተያየትና ተጽዕኖ ብሎ ነገር አይገባውም፤ አያገባውም።




> በተጠቀሰው የውይይት መድረክ ላይ ያደረጉትን ንግግር ተከትሎ አቶ ኃይለማርያም ወሳኝነታቸውን አሳይተዋል ሲባል ተሰምቷል። ውኃ የማይቋጥር ደካማ አስተያየት ነው

## ራሱን የሚያርም ድርጅት?


የኢሕአዴግ ነባር አመራሮች በተደጋጋሚ ‹‹ኢሕአዴግ ራሱን በራሱ የሚያርም ድርጅት ነው›› ሲሉ ይሰማል። ማንም ሳይነግረው የራሱን የውስጥ ችግሮች ራሱ ነቅሶ እያወጣ ምህረት የለሽ በሆነ ግምገማው አባላቱን እያፋጠጠ ራሱን የሚያጸዳና የሚያጠናክር ድርጅት ስለመሆኑም ብዙ ተብሏል። በእርግጥም ኢሕአዴግና ስብሰባ፣ ኢሕአዴግና ግምገማ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። ድርጅቱ እንደተለመደው የዘመቻ መርሐ-ግብሮችን ከነደፈ በኋላ ከላይ እስከ ታች ግምገማ ይያዛል። ‹‹አሁን በያዝነው መንገድ ከሄድን ህልውናችን ጥያቄ ውስጥ ይገባል፤ መልካም አስተዳደርን የማስፈን ጉዳይ የህልውና ጉዳይ ነው›› ይባልና ለተፈጠሩት ችግሮች ተጠያቂ የሚሆን አካል ይፈለጋል። እንደተለመደው ሁሉም ‹‹አጥፍቻለሁ፤ ችግሩ ይመለከተኛል፤ ይገልጸኛል›› እያለ ይወጣል። ሕዝብ የተማረረባቸው ካድሬዎች ሁሉ በለቅሶ ጭምር ‹‹ድርጅቴን በድያለሁ›› እያሉ ‹‹ሂሳቸውን ያወርዳሉ።››

የኢሕአዴግ የሥልጣን መሠረት የጥቅም ግንኙነት ነውና እነኝህ ሕዝብን ያስለቀሱ ኃይሎች ለፈጸሙት ጥፋት ክስ ቀርቦባቸው ተመጣጣኝ ቅጣት ማግኘት ሲገባቸው ‹‹ጥፋታቸውን ሂስ በማደረጋቸውና ለወደፊቱ ከጥፋታቸው እንደሚማሩ ቃል በመግባታቸው›› ይታለፋሉ። የተማረረባቸውን ሕዝብ ለማስደሰት ሲባል ካሉበት ኃላፊነት ተነስተው ወደሌላ አካባቢና ወደሌላ ሹመት ይዛወራሉ። የኢሕአዴግ ራስን ማረም ከዚህ የዘለለ አይደለም።

## የአቶ ኃይለማርያም ወሳኝነት

በተጠቀሰው የውይይት መድረክ ላይ ያደረጉትን ንግግር ተከትሎ አቶ ኃይለማርያም ወሳኝነታቸውን አሳይተዋል ሲባል ተሰምቷል። ውኃ የማይቋጥር ደካማ አስተያየት ነው። ለምን? አንደኛ፣ አቶ ኃይለማርያም በዕለቱ ከዚህ ቀደም ያልተባለ አዲስ ነገር አልተናገሩም። አቶ መለስ ‹‹ኢሕአዴግ በስብሷል፤ በስብሰናል›› ብለውን እንደነበር ይታወቃል። ዓላማው አንድ ቢሆንም የአቶ ኃይለማርያም ንግግር በይዘትም በቅርጽም ከአቶ መለስ ንግግር ያነሰ ነው። ሁለተኛ፣ ሕገ መንግሥቱ ከፍተኛ ሥልጣን የሚያጎናጽፋቸው ቢሆንም አሁን ባለው የአገራችን የፖለቲካ ኬሚስትሪ አቶ ኃይለማርያም ወሳኝ ሊሆኑ የሚችሉበት አንዳችም መንገድ የለም። ወሳኝነታቸውን አሳይተዋል የሚለው አገላለጽ ተራ ማደናገሪያ ነው። ለነገሩ እርሳቸውም የአቶ መለስን ሌጋሲ የማስቀጠል እንጂ ወሳኝ የመሆን ዓላማ እንደሌላቸው ገና ከጠዋቱ ግልጽ አድርገዋል። ሰውየው የሌላቸውን ርዕይ እነኝህ ወገኖች ከየት አምጥተው ሊያሸክሟቸው እንደሚፈልጉ ጨርሶ ግልጽ አይደለም።

ነጻ አስተያየት



መስከረም አበራ

# "እያመረቱ መራብ፤ "እየተቀለበ" መክሳት . . . ?

‹‹የምሥራቅ አፍሪካ የውኃ ገበቴ›› የምትባለዋ አገራችን ድርቅ ከመቅጽበት ወደ ረኀብ የሚቀየርባት የተፈጥሮ ሀብት ሳይሆን የሁነኛ መሪ ደኀ በመሆኗ ነው:: ከዘመነ ኢሕአዴግ በፊት የነበሩ ገዥዎች የሕዝብ ረኀብ ከፌሽታቸው የማያናጥባቸው ልበ-ደንዳና አምባገነኖች ነበሩ:: የሕዝብ ልጅ ነኝ ባዩ ኢሕአዴግም በትግል ዘመኑ አንዱ ሕዝብን የሚያታግልበት አጀንዳ ይኼው አገሪቱን እያሰለሰ የሚኀበኛት ረኀብ ነበረ:: ሸማቂው ኢሕአዴግ መንግሥት ከሆነ በኋላ የዴሞክራትነቱ ነገር ሥልጣን ላይ ለመሰንበት ካለው ብርቱ ፍላጎቱ ጋር አልገጥም ሲለው ልማታዊ ነኝ ካለ አንድ አሥርት እያለፈው ነው:: ልማታዊነቱን ለማጉላት ደግሞ የአገርን አኮኖሚ የመነደግኩ የድህነት ጠላት ነኝ ሲል አይደክመውም፤ ሰሚም የሚሰለቸው አይመስለውም:: የኢሕአዴግ የልማታዊ መንግሥትነት ነኝ ባይነት እርሱ እንደሚያወራው ድህነትን ከማጥፋት ይልቅ ሥልጣንን ከማስረዘም ፍላጎት ጋር ይዛመዳል:: ለዚህ ማስረጃው ብዙ ነው:: ማንም ሊክደው የማይችለው ዋና ማስረጃ ግን ልማታዊ ነኝ የሚለው ኢሕአዴግ ድርቅን ወደ ረኀብ እንዳይቀየር ማድረግን አለመቻሉ ነው:: በኢሕአዴግ የሥልጣን ዘመን ሁሉ የአገራችን ስም ከዓለም አሥር ዋነኛ የእርዳታ እህል ተቀባይ አገሮች ዝርዝር ጠፍቶ አያውቅም:: በዚሁ በኢሕአዴግ ዘመን ኢትዮጵያችን ብዙ ጊዜ ከአፍሪካ አንደኛ የእርዳታና ብድር ተቀባይ አገር ነች:: አሜሪካና እንግሊዝ አገራችንን አመዛኙን የእርዳታቸውን መጠን እንድትወስድ ያደረጉት የእድገቷን ብሥራት ሳይሆን ችግሯን ብርታት አይተው ነው:: ይህ ደግሞ ከአጼዎቹም ሆነ ከደርግ የተለየ ኢኮኖሚያዊ ተዓምር አምጥቻለሁ የሚለውን የኢሕአዴግ ፉከራ ተዓማኒነት ያሳጣዋል:: ኢሕአዴግ ከቀደምቶቹ የሚለይው ሰሚ አመነም አላመነ፤ ተግባር መሰከረም አልመሰከረ ለራሱ የልማታዊነት ፀዳልን ማጎናጸፉ ብቻ ነው::

ኢሕአዴግ ከዴሞክራሲያዊነት ይልቅ ልማታዊነትን የመረጠበት ምክንያት የፖለቲካ ዘይቤው እያደር ታገልኳቸው የሚላቸውን ቀደምቶቹን እየመሰለ በመሄዱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ማምጣቱን በመስበክ ከቀደምቶቹ መሻሉን ለማሳየት ነበር:: በርግጥ አጥብቆ ለማይጠይቅ ሰው ኢሕአዴግ ከዴሞክራሲ ይልቅ ልማትን አመጣሁ በማለት ከቀደምቶቹ መሻሉን ቢናገር አድማጭ አያጣም:: ገዥው ግንባር ይህን ሲል ብዙ ጊዜ ምስክር የሚያደርገው ባለፉት መንግሥታት ያልተሠሩ ፎቆችን፣ መንገዶችን፣ ግድቦችን ወዘተ. በመጥቀስ ነው:: እነዚህ ግንባታዎች የውጭ ብድርና እርዳታ ባይኖር ይሠሩ ነበር ወይ ለማለት፣ ግንባታዎቹ ሲከናወኑ አገርን ለማስያዝ የደረሰ እዳ እላይችን ላይ ተጭኖብን እንደሆነ ለመሞገት ለመጠየቅ የተዘጋጀ መንግሥት ያስፈልጋል:: መጠየቅን አርቆ የቀበረው መንግሥት ታዲያ አገሪቱን ለተከታታይ አሥር ዓመት በሁለት አሃዝ እድገት መነደግኳት እያለም አገራችን በረኀብ ክፉ ጥላ ሥር ትገኛለች:: የልማት ቆሌ ነኝ የሚለው ኢሕአዴግም እድገትን በሚዘምርበት አፉ 8.2 ሚሊዮን ሕዝብ ሊሞትብኝ ስለሆነ ስንዴ ጭናችሁ ድረሱልኝ እያለ ነው::

ረኀቡ የመንግሥት ችግር አይደለም ለማለትም ደጋግሞ የረኀቡ መንስኤ ‹‹ኤልኒኖ›› የተባለው የውቂያኖስ ውኃ መሞቅ ያመጣው የአየር ንብረት መዛባት ነው ይላል:: እዚህ ላይ ልማታዊነት ከዝናብ ጥገኝነት መላቀቅ እንደሆነ ለመጠየቅ ሰሚ ጆሮ ማግኘት ግድ ነው:: ከዝናብ ጥገኝነት ሳይላቀቁ በሁለት አሃዝ ማደጌ ይቀጥላል ማለቱ ተዓማኒነት ይኖረዋል ወይ ለማለት መንግሥት ፕሮፖጋንዳን ከሃቅ የመለያ ቀልብ ያሻዋል:: እድገትና ረኀብ እንዴት አብረው ሊሄዱ ይችላሉ? የረኀብ መንስኤው ድህነት እንደሆነ ወዲህ ወዲያ የማያስብል ሃቅ ነው:: ሆኖም ኢሕአዴግ አይበገርምና የኑሮ ውድነት የእድገቱ ውጤት ነው ሲለን እንደኖረው ሁሉ ረኀቡም መንስኤው እድገት ነው እንዳይል ስጋት አለኝ!

## የምግብ ፖለቲካ

ምግብ ማግኘት የዜጎች መብት ሲሆን መንግሥት ደግሞ ዜጎቹን መመገብ ግዴታው ነው:: ሕዝቡን በተገቢ ሁኔታ መመገብ መቻል መንግሥትን መንግሥት ነኝ ብሎ ወንበር ላይ ለመቆየት ማስተማማመኛው ነው:: ይህ አሁን ቀርቶ ከክርስቶስ ልደት በፊት የኖሩ መንግሥታት ሲያከናውኑት የነበረ ዋነኛ የመንግስት ተግባር ነው:: በጥንታዊት ግብጽ ፈርኦኖች ለክፉ ቀን ሕዝባቸውን የሚመግቡት ትልቅ የምግብ ክምችት እንደነበራቸውና ረኀብ ሲከሰት ሕዝባቸውን ከክምችታቸው ይመግቡ እንደነበር የታሪክ መዛግብትም መጸሐፍ ቅዱስም ይተርካሉ::

> ኢሕአዴግ የመሬት ፖሊሲውን ለመቀየር በጄ ባይልም የግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግር እንደሚያስፈልገው ግን ያምናል። ከላይ እንደተገለጸው የግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲያመጣ የመሬት እና የግብርና ፖሊሲው መቀየር አለበት

በተመሳሳይ በጥንታዊት ግሪክና ሮም ድርቅ ወይም ጦርነት የምግብ እጥረት ባስከተለ ወቅት ለድሆች ዳቦና የጥራጥሬ እህል ይታደል እንደ ነበር መዛግብት ያትታሉ:: ይህ የሚሆነው ከመንግሥታቱ ቸር ለጋስነት የተነሳ ሳይሆን ለረኀብ መልስ ያልሰጠ መንግሥት ዕድሜ እንደማይኖረው ያኔም ይታወቅ ስለነበረ ነው::

ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩ መንግሥታት የተረዱትን ይህን እውነት የእኛ መንግሥታት በሃያኛው ክፍለ ዘመንም መረዳት ተስኗቸው የኢሕአዴግ ቀደምቶቹ አጼ ኃይለ ሥላሴና ደርግ ረኀብን መደበቅን ይመርጡ ነበር:: በሽታውን የደበቀ መድሃኒት የለውምና የደበቁት በሽታ ግበዓተ መሬታቸውን አፋጠነው:: ከዚህ በሽታ ሙሉ በሙሉ የተዋጀ የማይመስለው ኢሕአዴግም እንደ ቀደምቶቹ ረኀቡን ሸምጥጦ ባይክድም በረኀብተኛ ቁጥር ላይ ሳይነታረክ አይሆንለትም:: አሁን አሁን ያመጣው ዘይቤ ደግሞ ‹‹ችግር ቢኖርም ከቁጥጥር ውጭ አይደለም፤ ከክምችት እህል ከልሆነም በግዥ ሕዝባችንን መመገብ ስለምችል እርዳታ አንፈልግም›› የሚል ለቅጸፈት የሚሰጥ የማያዛልቅ ፀሎት ነው:: ይህ የቁጥር ንትርኩንም ሳይተው ያመጣው አዲስ ፈሊጥ ነው:: ነገሩ ልማታዊ ነኝ ባልኩበት አፌ እንዴት እለምናለሁ ከሚል አጓጉል መግደርደር የመጣ ነው:: ነገሩ ሊደብቁት የማይችሉት ነገር ነውና የተረጅውን ቁጥር በቅጽበት በእጥፍ አሳድጎ ድረሱልኝ ለማለት ተገዷል:: ተጠያቂነት የለም እንጅ መንግሥት የሚጠየቅ ቢሆን የተረጅዎችን ቁጥር ከ4 ሚሊዮን በአንድ አፍታ ወደ 8.2 ሚሊዮን ያሳደገው እንዴት እንደሆነ ልማታዊነቱስ እርዳታ ከመለመኑ ጋር እስከመቼ አብሮ እንደሚሄድ መጠየቅ ነበረበት:: እንደሚታወቀው ኢሕአዴግ ለአርሶ አደሩ የቆምኩ በመሆኔ የአርሶ አደሩን ሕይወት በእጅጉ ለውጫለሁ ባይ ነው:: ሚሊየነር አርሶ አደሮች አፍርቻለሁ ሲል ብዙ ሜዳሊያዎችን በከሲታ አርሶ አደሮች ቀጭን አንገት ላይ አጥልቆ አሳይቶናል:: ምግብ ለሥራ፣ የምግብ ዋስትና፣ በምግብ ራስን መቻል የሚሉ ተግተልታይ ፕሮግራሞችን ነድፎ ብዙ ብዙ ተናግሮላቸው ሰምተናል፤ ውጤታቸው ግን ምግብ ከመለመን ታድጎን አላየንም::

በምግብ ራስን መቻል የሚለው ጽንሰ ሐሳብ በግርድፉ በአገር ውስጥ በሚመረት ምርት ሕዝብን መመገብን የሚያሳይ ሲሆን የምግብ ዋስትና የሚለው ነገር ከውጭ በተገዛም ይሁን በአገር ውስጥ በተመረተ እህል ሕዝቡን ያለ እህል እጦት ስጋት ተገቢውን አልሚ ምግብ የያዘ ምግብ መመገብን ያመለክታል:: የምግብ ዋስትናም ሆነ በምግብ ራስን መቻል የአንድ አገርን እድገት የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው:: በምግብ ራስን ለመቻል የአንድ አገር የግብርና መስክ ማደግ አለበት:: የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ብዙ አገሮች በምግብ ራስን መቻልን እንደ ዋነኛ መንገድ ይወስዱታል:: በምግብ ራሳቸውን የቻሉ ምርታማ አገሮች ብዙ ጊዜ በአገራቸው ትርፍ ማምረት ይችላሉና ድርቅ ከመከሰቱ በፊት በቂ የምግብ ክምችትን ያዘጋጃሉ:: ይህ ክምችት ምናልባትም ከአንድ አሥርት ዓመት ለዘለለ ጊዜ ዜጎችን የሚመግብ ሊሆን ስለሚችል ድርቅ በቶሎ ወደረኀብ አይቀየርም:: ይህን ለማስቻል የግብርናው መስክ ምርታማነት ወሳኝ ነው:: ለግብርና ምርታማነት ደግሞ የመሬትና የግብርና ፖሊሲ ዋነኛ ጉዳይ ነው::

## የቴክኖሎጂ ሽግግር ነገር. . .

የመሬት ፖሊሲውን የመከለስ ጥያቄ ሲነሳበት ሞቴን ያቅርበው የሚለው ኢሕአዴግ ልማታዊነቱን እያወራም ድርቅ ረኀብን እንዳያመጣ መከላከል የተሳነው በዚሁ በመሬት ፖሊሲው ላይ ባለው ገታራ አቋም ነው:: የበሬ ግምባር በምታክል መሬት ላይ ተዓምር የሚሠሩ አርሶ አደሮችን አፍርቻለሁ ባዩ ኢሕአዴግ ግብርናው ቁርጥራጭ መሬት በያዙ ደሃ አርሶ አደሮች ብቻ እንዲዘወር አድርጓልና በግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ አልተቻለም:: የቴክኖሎጅ ሽግግር ባለመኖሩ እስከዛሬ በአጼ ኢዛና ዘመን ይደረግ እንደነበረው ሁለት በሬ ከአንድ ማረሻ ጋር ተቀይዶ በደሃ አርሶ አደር ቀጭን እጅ ይገፋሉ:: እንዲህ ታርሶ ወደ ዘጠና ሚሊዮን የሚጠጋ ሕዝብ በልማት ተምነሸነሸ ተብሎ ይደሰኮራል:: ውጤቱ ግን እንደ ዲስኩሩ አያማልልም:: ይልቅስ በአንድ ሳምንት ልዩነት ውስጥ የተረጅ ቁጥርን እየቀያየሩ ድረሱልኝ የሚያስብል አንገት አስደፊ ነው::

በአገራችን እንደ ግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ያልተደረገበት መስክ ያለ አይመስለኝም:: ለናሙና ያህል የአገራችንን የመገናኛ፣ የመዝናኛ፣ የግንባታ፣ የሕክምና ኢንዱስትሪ ያየን እንደሆን ከቅርብ ዓመታት ጋር ብናወዳድር እንኳን የምናየው ለውጥ አናጣም:: በግብርናው ዘርፍ ያየን እንደሆን ግን በገበሬው ልክ ሊቆጠሩ የደረሱ የልማት ሠራተኞችን ከመመደብ ባለፈ የሚታይ የቴክኖሎጂ ሽግግር አልታየም::

በግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር ታይቷል ለማለት ቢያንስ በበሬ ማረስ ቀርቶ በትራክተር ሲታረስ፣ እህል ለመውቃት እንስሳት አሰልፎ ማስረገጥ ቀርቶ ለዚሁ በተዘጋጀ ማሽን ሲወቃ፣ ጥንታዊው ሰው እርሻ በጀመረ ዘመን ያደርግ እንደነበረው ዝናብ ሲዘንብ ጠብቆ በዓመት አንድ ጊዜ ከማምረት ዓመቱን ሙሉ ሲመረት ማየት አለብን:: ይህን ለማድረግ ደግሞ ትላልቅ የመስኖ እርሻዎች መኖር አለባቸው:: ይህ ገቢራዊ ይሆን ዘንድ መሬት በተቆራረጠ ሁኔታ በአርሶ አደሩ እጅ ብቻ ይያዝ የሚለው የኢሕአዴግ ገታራ የመሬት ፖሊሲ መከለስ አለበት:: በትራክተር ለማረስ ሰፊ መሬት ያስፈልጋል:: መስኖ ተጠቅሞ ዓመቱን ሙሉ ለማምረትም ሰፋፊ መሬቶች ተሻይ ናቸው:: አዳዲስ ቴክኖሎጂን ተጠቅሞ ምርታማነትን ለማሳደግ የኢኮኖሚ አቅም ያስፈልጋል:: ይህ ደግሞ ቁርጥራጭ መሬቶችን ከሚይዙ ደሃ አርሶአደሮች ይልቅ የትላልቅ የእርሻ መሬቶች ባለቤቶች ለሆኑ ባለሀብቶች ይቀላል:: ምርታማነት የሚረጋገጥበት የቴክኖሎጂ ሽግግር እውን የሚሆነው አገራችንን እየመራ ያለው መንግሥት የግብርናና የመሬት ፖሊሲውን ለመከለስ ሲፈቅድ ብቻ ነው:: ይህ ግን የሚሆን አይመስልም:: ምክንያቱም ኢሕአዴግ የመሬት ፖሊሲውን እንደማይቀይር ሲናገር ፈርጠም ብሎ ይህ የሚሆነው በመቃብሬላይ ነው ብሏልና::

ይህን የሚለው ያው ሥልጣንን ለማራዘም ካለው ጽኑ ፍላጎት የተነሳ ነው:: ኢሕአዴግ በጻፈው ሕገ መንግሥት መሬት የሕዝብና የመንግሥት ነው ሲል ይደነግጋል:: በተግባር ግን ራሱን የመሬት ሰጭ ነሽ ባለቤት አድርጎ የአጼዎቹን ዘመን የሰው የመሬት ከበርቴነት በመንግሥት የመሬት ከበርቴነት ተክቷል:: ይህ ደግሞ ብቸኛ የህልውና ምንጩ የሆነውን መሬቱን እንዳይነጠቅ የሚሰጋው አርሶ አደር ኢሕአዴግን እያባበለ ይሁን እየተለማመጠ እንዲኖር ደርጋል:: በዚህ ላይ ማዳበሪያውና ምርጥ ዘሩም በብቸኝነት በመንግሥት የሚሰፈር ስለሆነ አርሶ አደሩ ኢሕዴግን ከመፍራት ጋር እንዲለማመጠው ይገደዳል:: የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ኢሕአዴግ የዘወትር በገጠሩ የአገራችን ክፍል በምርጫ ‹‹እንዲያሸንፍ›› ያደርገዋል:: የአገራችን ሕዝብ አብዛኛው ቁጥር ደግሞ በገጠር ነዋሪ መሆኑ ለኢሕአዴግ ሥልጣን ዘላለማዊነት ወሳኝ ነው::

ኢሕአዴግ የመሬት ፖሊሲውን ለመቀየር በጄ ባይልም የግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግር እንደሚያስፈልገው ግን ያምናል:: ከላይ እንደተገለጸው የግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጅ ሽግግር እንዲያመጣ የመሬት እና የግብርና ፖሊሲው መቀየር አለበት:: ኢሕአዴግ ግን ይህን ሃቅ ሸሽቶ የመሬት ፖሊሲው ሳይቀየር የቴክኖሎጂ ሽግግር ይመጣል ብቻ ሳይሆን መጥቷል ለማለትም ይቃጣዋል:: ይህን በተመለከተ በአንድ ወቅት አቶ መለስ ያስደነገጠኝን ንግግር ተናግረዋል:: እንዲህ አሉ አቶ መለስ ‹‹በአገራችን የግብርናው ዘርፍ የቴክኖሎጂ ሽግግር አድርጓል፤ የዚህ ምስክሩ ድሮ ዝም ብሎ ሲያመርት የነበረው አርሶ አደር እኛ የግብርና ባለሙያ ከመደብንለት ወዲህ ምን ባመርት ገበያላይ ብዙ ገንዘብ ያወጣልኛል፣ አምና ምን ተወዶ ነበር ብሎ መርምሮ ማምረት መጀመሩ ነው":: ይህን ነገር የተናገሩት አቶ መለስ እውን የግብርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ይህ ነው ብለው አምነው፣ አርሶ አደሩም ገበያ ጠይቆ ማምረት የጀመረው ኢሕአዴግ ከመጣነው የሚለውን እውነት ነው ብለው አይመስለኝም:: ይልቅስ የመሬት ፖሊሲውን መቀየር ግድ የሚለውን የግብርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ጉዳይ ፖሊሲውን ሳንቀይር ማድረግ እንችላል ለማለት ታስቦ የተነገረ ተለምዷዊው ብልጣብልጥ አካሄድ ነው:: ለነገሩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፓርላማ መጥፋት የመድበለ-ፓርቲ ማበብ ምልክት ነው ካሉት አቶ መለስ አንደበት ይህ ቢሰማ አይገርምም::

# እንግዳ

# "በዓለም ታሪክም ያለመስዋዕትነት ወደ ዴሞክራሲ የተሸጋገረ አገር የለም"

## አቶ ማሙሸት አማረ



**ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ ለእስር እንደተዳረጉ ይታወቃል። እስኪ ካለፉት ሃያ አራቱ ዓመታት ውስጥ ምን ያህሉን በእስር ላይ እንዳሳለፉ እና አያይዘው እንዴት ወደ ፖለቲካ ትግል እንደገቡ ይግለጹልን።**

ኢሕአዴግ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ አብዛኛውን ጊዜ ያሳለፍኩት በእስር ቤት ውስጥ ነው:: ከትንሹ 10 ሰዓት እስከ ትልቁ ስምንት ዓመት ድረስ የሚረዝም ከእስር ጊዜ በላይ ታስሬያለሁ:: እንግዲህ ጊዜያቱን ስንደምራቸው በ1980ቹ ጀምሮ 8 ዓመታት ታስሬያለሁ፤ በቅንጅት ዘመን እንደሌሎቹ አመራሮች እኩል 2 ዓመት ለሚጠጋ ጊዜ (ሃያ ሁለት ወራት) ታስሬያለሁ፤ 10 ሰዓትም፣ አንድ ሙሉ ቀንም፣ ሁለት ወርም የታሰርኩበት ጊዜ አለ:: አሁን በቅርቡ እንኳን ከአራት ወር እስር በኋላ ነው የወጣሁት:: እነዚህን ሁሉ ጊዜያት ብትደምራቸው ኢሕአዴግ በሥልጣን ላይ ከቆየባቸው ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ ወደ አሥራ አንድ ዓመቱን በእስር አሳልፌያለሁ ማለት ነው::

ወደ ፖለቲካ ትግል የገባሁት ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ ወያኔ፣ ሻዕቢያና ኦነግ በአንድ ላይ ሆነው በመላ አገሪቱ በተለይ ደግሞ በሐረረጌና በአርባ ጉጉ ያሉ አማሮችን ሲጨፈጭፉ ሕዝቡን ማዳን ስለነበረብን ሚያዚያ 15 ቀን 1984 ዓ.ም. የዩምቨርሲቲ ትምህርቴን አቋርጬ ከመአሕድ ጋር ተቀላቀልኩ:: ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አማራውን ለማዳንና የኢትዮጵያንም አንድነት ለመጠበቅ ከሌሎች ጓደኞቼ ጋር ሆኘ የምችለውን ሁሉ አድርጌያለሁ:: ለመጀመሪያ ጊዜ የታሰርኩትም በሰኔ 1984 ዓ.ም. በሰሜን ሸዋ እነዋሪና ጅሁር (ሞረትና ጁሩ ወረዳ) መአሕድ ሕዝባዊ ስብሰባ ሲያደርግ እኔ ነበርኩ የማስተባብር:: በጣም ትልቅ ሕዝብ መሰብሰብ ችለን ነበር:: የአማራው ሕዝብ በአፋር፣ በባሌ፣ በአርሲና በሐረርጌ እየደረሰበት ያለውን ግፍ ሁሉ ለሕዝባችን አስረድተናል:: የሕዝቡ ቁጣ ከፍ ያለ ነበር:: ከዚያ መንግሥት ሕዝብ አነሳስተሓል ብሎ ሰኔ 30 ቀን 1984 ዓ.ም. እነዋሪ ከተማ ከሌሎች 5 ባልደረቦቼ ጋር ለ10 ሰዓት ያክል እስር አሀዱ አልን:: በጊዜው በሁሉም የሰሜን ሸዋ አካባቢዎች በመንቀሳቀስ መአሕድ ሕዝባዊ ተቀባይነት እንዲኖረው የቻልነውን ያክል አድርገናል::

ታህሣስ 11 ቀን ደብረ ብርሃን የአጼ ዘርዓያቆብ አደባባይ ላይ በፕሮፌሰር አሥራት መሪነት እጅግ በጣም ትልቅ የተባለ ሕዝባዊ ስብሰባ አደረግን:: ፕ/ር አሥራትም እኛም ሕዝብ ቀስቅሳችኋል ተብለን ታሰርን:: እኛ ደብረ ብርሐን ፖሊስ ጣቢያ ሁለት ቀን ታስረን ተፈታን:: ይህ እንቅስቃሴ እያደገ ሂዶ ነው ሁሉንም የሰሜን ሸዋ አካባቢዎች በ9 ወር ውስጥ ያደረስነው:: ለገዢው አካል ይህ ታላቅ የራስ ምታት ነበር:: ያኔ ወያኔ ብቻውን አልነበረም:: ሻዕቢያም ኦነግም አብረውት ነበሩ:: የአማራውን መገደልና መታረድ እንዲቆም ከፍተኛ ትግል አድርገናል:: ሰኔ 1986 ዓ.ም. በአሳግርት በመቀስቀስና በማስተማር ላይ እንዳለን ሽብር እየፈጠራችሁ ነው ተብለን ተይዘን ለስምንት ዓመታት ከፕ/ር አሥራት ጋር ወህኒ ወረድን:: መጀመሪያ የታሰርኩት አሳግርት ጦር ካምፕ ነበር፤ ከአሳግርት ወደ ጠባሴ ካምፕ አመጡን:: ከጠባሴ ወደ ማዕከላዊ አምጥተውን 7 ወራት ካቆዩን በኋላ ከርቸሌ ስምንት ዓመት ተዘጋን:: ከፕ/ር ጋር አምስት ዓመታት ያክል አብረን እንደቆየን በጠና ታመሙ፤ እሳቸው ሕይታቸው ሲያልፍ እኛ ፍርዱን ጨርሰን ወጣን::

ከዚያ በኋላም መአሕድን ወደ መኢአድ እንዲቀየር ካደረጉት ሰዎች ውስጥም እኔ አንዱ ነኝ:: በመላ አገሪቱ እየዞርን ሰፊና ኢትዮጵያን ያማከለ ሕዝባዊ ፓርቲ እንዲሆን አድርገናል:: በ1997 ዓ.ም. ከሌሎች ሦስት ድርጅቶች ጋርም ሆኖ ቅንጅትን ሲፈጥር እኔም አብሬ ነበርኩ:: ማንኛውም የቅንጅት አመራር ያደረገውን ያክል እኔም ደክሜያለሁ:: ሕዝብን አብረን ቀስቅሰናል፣ አስተምረናል፤ መርተናል:: በ1997 ዓ.ም. ምርጫ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በተወለድኩበት አካባቢ ተወዳድሬ የፓርላማ ወንበር አሸንፌም ነበር:: ሆኖም ኢሕአዴግ የሕዝብን ድምጽ እየቀማ ምርጫውን ሲያበላሸው ቅንጅት ወደ ፓርላማ ላለመግባት ሲወስን እኔም ከቅንጅት የላዕላይ አመራሮች አንዱ እንደመሆኔ ውሳኔውን አክብሬ ፓርላማ ሳልገባ የሕዝብ ድምጽ እንዲመለስ አብሬ ጥሪ አቀርቤያለሁ:: የቅንጅት አመራሮች በሙሉ በማዕከላዊና በቃሊቲ ለ22 ወራት አብረን ታስረን ነው የወጣነው:: ከእስር ስንወጣም በቅንጅት መካከል ስምምነት ስላልነበር መኢአድን ወደነበረበት ለመመለስ ከፍተኛ ጥረት አድርገናል:: የነበሩ ቢሮዎችን እንዲከፈቱ አድርገናል::

በዚሁ ሁሉ ትግል ተጠቅሜያለሁ ብዬ ካሰብኩ እንደ ሕዝብ እንጂ እንደ ግለሰብ አይደለም:: ወያኔ፣ ሻዕቢያና ኦነግ በዘር ላይ አነጣጥረው አማራውን ሲጨርሱ በከፈልነው ከፍተኛ መስዋዕትነት የተወሰነም ቢሆን እንዲቆም አድርገናል:: ሁለተኛው ማንም የፖለቲካ ፓርቲ ባልነበረበት ወቅት እኛ ስለዴሞክራሲ፣ ሰላም፣ ነጻነትና ስለሕግ የበላይነት ያስተማርነው ትምህርት ነው ዜጎችን በምርጫና በሰላማዊ መንገድ መንግሥት ይቀየራል የሚል እሳቤን ያሰረጹ:: ስለዚህ በእኛ ምክንያት በመጡ ለውጦች ደስተኛ ነኝ::

በግሌ ያጣሁት ነገር እጅግ ብዙ ነው:: እንደ ግለሰብ ካሰብነው ያላጣሁት ነገር የለም ማለት ይቻላል:: በአካሌ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶብኛል፤ ቤተሰቦቼ ተጎድተዋል:: ማኅበራዊ ሕይወቴን ሊያበላሹት ሞክረዋል:: ትምህርት እንኳን በየዘመኑ እያሰሩ ከትምህርቴም ለማስተጓጎል ሞክረዋል:: የኔውን ተወው:: እናትና አባቴ እንኳን የፀረ ኢሕአዴግ ወላጆች ናችሁ ተብለው መሬት እንኳን እንዳያገኙ ተደረገዋል:: እህቶቼና ወንድሞቼ በእኔ ምክንያት ከመንግሥት መሥሪያ ቤት ተባረዋል:: በዚህ ዘመን የተሰቃየውና የሚሰቃየው ብዙ ቢሆንም በጉዳት እንደኔ ቤተሰቦች ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት የለም ማለት እችላለሁ:: ይሁን እንጂ ደግሞ ጫናው ከፍተኛ ቢሆንም ባደረግኳቸው ነገሮች ሁሉ አልከፋም:: ምክንያቱም ይህ የአገርና የሕዝብ ጉዳይ ነውና ነው:: ወገንህ እየታረደና እየተፈናቀለ ዝም ብሎ መመልከት ለእኔ የሰው ልጅ ሰዋዊ ባሕሪ ነው ብየ አላስብም:: ሰው ሲበደል ለምን ማለት ያስፈልጋል::

> <<ከጠመንጃ አፈሙዝ ውስጥ ዴሞክራሲም፣ የሕግ የበላይነትም፣ ልማትም የለም፤ ያለው አፋኝነትና አምባገነናዊነት ብቻ ነው>>

**ከትግል ተመክሮዎ ተነስተው ስለአገራችን ፖለቲካ ያለዎት ግምገማ እና ትግሉ አስገኘው የሚሉት ስኬት ምንድን ነው?**

መሰደድ፣ መገደል፣ መገረፍ፣ ንብረት መዘረፍ፣ መታሰር እንዲሁም አጠቃላይ የሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን መነጠቅ ሁሉ በአምባገነናዊ ሥርዓት ውስጥ ትግሉ የሚጠይቃቸው ነገሮች ናቸው:: ይህ ሥርዓት ምንም ይሁን ምን ፍጹም የሆነ አምባገነን እንደሆነ ግልጽ ነው:: ይህን አምባገነናዊ ሥርዓት ለመቀየር እነዚህን የመሰሉ ዋጋዎችን መክፈል የግድ ነው:: ውጤቱም ቀላል አይደለም:: ሕዝብ የኔ የሚለውን የመምረጥ፣ ለሕግ የበላይነትና ዴሞክራሲ የመታገል ባህል መኖሩ በራሱ ትልቅ ውጤት ነው:: በምርጫ 1997 ዓ.ም. የታየው የሕዝብ መነሳሳትና አገራዊ ፍቅር ዝም ብሎ በዋዛ የመጣ አልነበረም:: ትልቅ ዋጋ ተከፍሎበታል:: ያን ስሜት ማምጣት በራሱ ትልቅ ነገር ነው:: ሥልጣን ስላልተያዘ ብቻ ዋጋ የለውም ልንል አንችልም:: ዋናው ግባችን ይህን አምባገነናዊ ሥርዓት በዴሞክራሲያዊ አገዛዝ መቀየር ቢሆንም እስካሁን በሕዝብ ንቅናቄ የተመዘገቡት ለውጦች የዚያ አካል ናቸው ብዬ አምናለሁ:: ሥርዓቱ አፋኝነት የለየለት አምባገነን ስለሆነ ነው እንጅ ሕዝብ ይበጀኛል የሚለውን መርጧል:: በድምጽ መንግሥት መቀየር ይቻላል የሚለው እሳቤ መጥቷል:: ይህ ሁሉ መገደል፣ መሰደድና ሌላም ነገርን ብንፈራ ኖሮ ዝም ብሎ በዋዛ ሊመጣ አይችልም:: በዓለም ታሪክም ማንም አገር ያለመስዋዕትነት ወደ ዴሞክራሲ የተሸጋገረ የለም::

ይህ ሥርዓት ሕዝባዊ ፍቅርና ወገንተኝነት የለውም፤ ራሱም ያውቃል:: ሕዝብ እኮ ስለአገር ጉዳይ ማዳመጥ የሚፈልገው ተቃዋሚውን ጎራ ነው:: ለምን ሕዝብ ከመንግሥት ይልቅ ሥልጣን ያልያዘውን አካል ማመን ፈለገ? ብለህ ስትጠይቅ በተደረገው ትግል ያገኘነው የሕዝብ አመኔታና ፍቅር ከፍተኛ መሆኑን ትገነዘባለህ::

**ከእስር የተፈቱት በቅርቡ ነው። ቀደም ብሎ ደግሞ በፓርቲያችሁ ውስጥ በተፈጠረ አለመግባባት ምክንያት ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሕጋዊነት የሚያውቀው የእርስዎን የድርጅት ሊቀመንበርነትና ካቢኔ ሳይሆን በአቶ አበባው መሐሪ የሚመራውን ቡድን መሆኑን ገልጾ እናንተን ማገዱ አይዘነጋም። በዚህ ሁኔታ የእርስዎ ቀጣይ የፖለቲካ እጣ ፈንታ ምንድን ነው? በፖለቲካ ትግሉ ይቀጥላሉ?**

በመጀመሪያ ደረጃ እኛ ትግል ስንጀምር በምርጫ ቦርድ መልካም ፈቃድ አይደለም የጀመርነው:: ሕዝባችንና አገራችን እንዴት እንታደጋለን ብለን የተነሳነው ምርጫ ቦርድ ከመምጣቱ በፊት ነው:: አሁን ምርጫ ቦርድ ሥልጣን ሰጪና ነሽ መሆን አይችልም:: ይህን የማድረግ የሕግ ማዕቀፍም የለውም:: በፓርቲዎች መተዳደሪያ ደምብም ሆነ በምርጫ አዋጅ ይህን ዓይነት ሥልጣን አልተሰጠውም:: ይህ የሆነው ምርጫ ቦርድ አንዱ የአምባገነኑ ሥርዓት ቀኝ እጅ በመሆኑ ብቻ የሆነ ነው:: የመኢአድ ጠቅላላ ጉባኤ የመረጠው እኛን እንጂ አቶ አበባውን አይደለም:: አቶ አበባው ባዶ ድንኳን ይዞ ተቀምጦ ይሆናል እንጅ መኢአድ በእኛ ልቦና ውስጥ ነው ያለው:: በአባላቶቻችንና በደጋፊዎቻችን ልቦና ውስጥ ነው ያለው:: ስለዚህ ይህን የአባላቶቻችንና የሕዝባችን ድጋፍ እስካለ ድረስ መኢአድ ይዞት የተነሳውን የሕዝብን ሥልጣን ባለቤትነት፣ የአገር ሉዓላዊነትና የዜጎች እኩልነት እስኪከበር ድረስ ትግላችን አይቆምም::

በአምባገነንና አፋኝ ሥርዓት ውስጥ የማይታሰብ የለምና ምርጫ ቦርድ ከልባችሁ መኢአድን አስወጣለሁ ብሎ ሊያስብ ይችላል፤ እንቅስቃሴያችንም የተገደበ ሆኗል፤ ደህንነታችንም አደጋ ላይ ሊወድቅ ይችላል ሆኖም እስትንፋሴ እስካለ ድረስ ትግል አላቆምም:: ምክንያቱም ትግላችን የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነውና:: ሰላምን፣ ነጻነትን፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሶ የመሥራት መብታችን መከበሩን እስከምናረጋግጥ ትግላችን አይቆምም::

**አንዳንድ ወገኖች በአገራችን የሰላማዊ ትግል ባጠቃላይ ባይሆንም የድርጅት ፖለቲካ አልቆለታል የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። የእርስዎ አስተያየት ምንድን ነው?**

ለእኔ ይህ አስተሳሰብ አስቀድሞ መሸነፍ ነው:: ሰላማዊ ትግል ከሌላው ትግል የበለጠ ዋጋ ያስከፍላል:: በሰላማዊ ትግል ሁልጊዜም መመታት፣ መታሰር፣ መገደል መሰደድ አለ:: ይህን ሁሉ አስቀድመን አምነን ነው ወደሰላማዊ ትግሉ የገባነው:: አንዳንድ ወገኖች የፖለቲካ ድርጅት አቋቁሞ መታገል ኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ አያመጣም ብለው የሚያስቡ አሉ፤ እነርሱ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

## የመጻሕፍት ዳሰሳ



ዓለማየሁ ገብረማርያም (ፕ/ር)

# ኢትዮጵያውያንን ከራሳቸው መጠበቅ

## በፕሮፌሰር መስፍን "አዳፍኔ" ላይ አንዳንድ ሐሳቦች

‹‹አዳፍኔ ፍርሃትና መክሸፍ›› በሚል ርእስ የታተመው የፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም አዲስ መጽሐፍ ዜጎች በብልሹ አስተዳደር፣ በአምባገነናዊ የአፈና አገዛዝና በሞራል ዝቅጠት ተዘፍቀው ከሚገኙበት አረንቋ ውስጥ ራሳቸውን በንስሃ በማደስ ከሃጢያት እንዲጸዱ የሚያሳስብ መጽሐፍ ነው:: በዚህ መጽሐፍ እውነታንና አመክንዮን በተላበሰ ድምጸትና አንደበት አገር ወዳዱ የምሁር ቁንጮና አርበኛ ፕ/ር መስፍን፣ በጎሳ ፖለቲካ ተዋቅሮ አገራቸውን እያተራመሰ በሚገኘው የደናቁርት ስብስብ እኩይ ድርጊት በከፍተኛ ደረጃ በመበሳጨት ይህንን አገር አውዳሚ የሆነ ድርጊት የአገር ተረካቢው ወጣት ትውልድ ፍቅርና ሰላም የሰፈነባት፣ እድገት በተጨባጭ የሚመዘገብባት፣ ሹመት በጎሳ መሥፈርትና በፖለቲካ ታማኝነት እየተዘገነ የሚታደል ሳይሆን በትምህርት ብቃትና ችሎታ የሚሰጥባት፣ ባለሀብትነት በማጭበርበርና የሕዝብን ሀብት በማንአለብኝነት በመዝረፍ ሳይሆን ነጭ ላብን አፍስሶ፣ አእምሮንና አካላዊ ብቃትን ተጠቅሞ ሀብት የሚፈራባት እንዲሁም ሙስና፣ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነት፣ የጥላቻ እና የበቀልተኝነት አስተሳሳብ፣ የሃይማኖት ጽንፈኝነት ወዘተ. የሚወገድባት አገር እንድትሆን ጥረት እንዲያደርግ ምሁራዊና አባታዊ ምክር ለመስጠት የሞከሩበት መጽሐፍ ነው::

ፕ/ር መስፍን በሥልጣን ማማ ላይ ተንጠልጥለው ለዘመናት ሕዝብ የሚያሰቃዩትን ኃይል አምላኪ አምባገነኖች ለበርካታ ዓመታት ምንም ሳይፈሩ ፊት ለፊት እውነታውን እስከ አፍንጫቸው ድረስ ሲናገሩ የቆዩና ያሉ ብርቅዬ ምሁር ናቸው:: ላለፉት አራት አሥርት ዓመታት የአፈና አገዛዝን ሲታገሉ የኖሩ የአደባባይ ምሁር ናቸው - መስፍን:: ይህ ‹‹አዳፍኔ›› የተባለው መጽሐፋቸውም አሁን በሥልጣን ላይ ለሚገኙትም ሆነ ለሌሎቹ ትክክለኛውን እውነታ የገለጹበት ሥራ ነው::

በ21ኛው ክፍለ ዘመን ምሁራን የሰው ልጆችን ነጻነትና እውቀት ለማበልጸግ እየወሰዱ ያለውን ተልዕኮ ከግንዛቤ በማስገባት ፕ/ር ኤድዋርድ ሰዒድ የተባሉ ምሁር፣ ‹‹በሥልጣን ላይ ላሉት አካላት እውነታውን መናገር ለመሰቃየት፣ መከራን ለመቀበል መዘጋጀትና ለፍትሕና ለርትዕ ሲባል የእምቢታ ድምጽን ከፍ አድርጎ በማሰማት በሥልጣን እርካብ ላይ ተቆናጥጠው ከሚገኙት ገዥዎች ጋር ቅራኔ ውስጥ መግባት ማለት ነው›› ብለው ነበር::

በተጠናቀቀው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምረው በኢትዮጵያ በሥልጣን ላይ ላሉ ገዥዎች ሁሉ እውነትን በአደባባይ ሲናገሩ የቆዩት መስፍን እስከአሁኗ ሰዓት ድረስ በዚኸው በትግላቸው ቀጥለዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ እየተቀበለ ላለው ስቃይና መከራ ዋና ምስክር የሆኑት ፕሮፌሰሩ፣ በዚህ እምነታቸውና በአመክንዮ ላይ በተመሠረተው ጽኑ አስተሳሰባቸው ምክንያት ከፍተኛ መስዋዕትነትን ከፍለዋል:: ያለፉትን ሁለት አገዛዞች ትተን ፕ/ር መስፍን እውነትን ፊት ለፊት በመናገራቸው እና በፖለቲካና የሰብአዊ መብት ጥበቃ እንቅስቃሴዎች ላይ ንቁ ተሳትፎ በማድረጋቸው ባለፉት 24 የሕወሓት አገዛዝ ዘመናት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በግፍ ታስረው ተንገላተዋል:: አገዛዙ መስፍን አገራቸውን ትተው እንዲሰደዱም ከፍተኛ ጥረት አድርጓል::

እ.ኤ.አ ሚያዝያ 2015 ፕሮፌሰር መስፍን በአንድ ድረ ገጽ ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ ‹‹… ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ በምሠራበት ወቅት ወያኔዎቹ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መልኩ አገር ለቀቅን እንድንሰደድ ወይም ደግሞ ወንጀል እድንሠራ የማስገደድ ድርጊት ይፈጽሙብን ነበር:: ስለራሴ ብናገር፣ እኔን ለምን እንደሚያስፈራሩኝ እርግጠኛ አይደለሁም::





**የመጽሐፉ ርእስ በራሱ በርካታ የተወሳሰቡ ስሜቶችንና ትርጉሞችን አካትቶ የያዘ ነው። <<አዳፍኔ>> የሚለው ቃል በአንድ በኩል የመቅበር ሂደትን የሚያሳይ ወይም ደግሞ አንድን ነገር አፈር ውስጥ መደበቅን የሚያመላክት ሲሆን የእሳት መጥፋትንና የቀረውን ፍም በአፈር ወይም ደግሞ በውኃ ማጥፋትን ሊገልጽም ይችላል**

በአሁኑ ጊዜ እያስፈራሩኝ ያሉት ምናልባትም እየኖርኩበት ያለውን አፓርትመንት በመፈለጋቸው ምክንያት እንደሁነ በእርግጠኝነት አላውቅም:: በእኔ ቤት ውስጥ ያሉ እና የወያኔ ሎሌዎች ትልቅ ዋጋ ያወጣሉ ብለው የሚያስቧቸው ነገሮች አሉ ከተባለ ምናልባትም በገብረ ክርስቶስ ደስታ የተሳሉ ሁለት ስዕሎች ብቻ ናቸው:: ከዚህ ውጭ ግን በቤቴ ውስጥ ሊገኙ የሚችሉት ለወያኔ ምንም ዓይነት ዋጋ ሊያወጡ የማይችሉት መጻሕፍት ብቻ ናቸው:: ስለሆነም እኔ በወያኔ እጅ እየተሰቃዬሁ ያለሁት አገሬን ትች እንድሰደድ ከመፈለግ ዓላማ የመነጨ ሊሆን ይችላል:: ይህንን ድርጊት በ1992 ዓ.ም. ሞክረውት ነበር:: ሆኖም ግን አልሠራላቸውም:: እኔን በዚህ መልኩ እያሰቃዩኝ ያሉበትን ምክንያት በእርግጠኝነት ማውቅ የማልችል ቢሆንም በአንድ በደህና ቦታ ላይ በተቀመጠ የወያኔ ሰው ግልጽ እንደተደረገልኝ በእኔ ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ የማሰቃየት ዘመቻ ተከፍቶብኝ ይገኛል::

ይህች አገር የአንድ በጥባጭ ወሮበላ ስብስብ ብቸኛ ሀብት ናት የሚል እምነት የለኝም:: ይህች አገር የተመሠረተችው በእኛ እናት እና አባት፣ በአያት እና ቅድመ አያቶች ነው:: ማንም ቢሆን እኔን አስገድዶ ከአገሬ በማባረር ስደተኛ ሊያደርገኝ ፍጹም አይችልም:: እንደ ኢትዮጵያዊነቴ ማንም ቢሆን እኔን በማስፈራራት መብቴን ነጥቆ ሊወስድም በፍጹም አይችልም:: ይህንን በፍጹም አልፈቅድም:: ለወያኔዎች ግልጽ እንዲሆንላቸው ያለኝን አቋም በአጽንኦ ልነግራቸው እፈልጋለሁ:: በሕይወት እስካለሁ የምኖረው፣ ስሞትም የምቀበረው በዚህችው በኢትዮጵያ ምድር ነው:: ለወያኔና ለሎሌዎቹ አንድ እውነታ መንገር እወዳለሁ:: እኔን የጥቃት ሰለባ ለማድረግ ሲሉ ሕገ ወጥ ድርጊትና ወንጀል ቢሠሩ ያለምንም ጥርጥር ነገ ከዚህ የበለጠ ታላቅ ስቃይና ቅጣት ይቀበላሉ:: እነዚህ ሥልጣናቸውን ከሕግ አግባብ ውጭ በሚጠቀም ነጹሐን ዜጎችን በመግደል ኃያል የሆኑ የሚመስላቸው ዕብሪተኞች አንድ ጊዜ ቆም ብለው ሊያስቡ ይገባቸዋል:: ማንም ሰው ሰውን በመግደል ድልን ሊቀዳጅ ይችላል፤ እንደዚሁም ማንም ሰው በመሞት ድልን በገዳዮቹ ላይ ሊቀዳጅ ይችላል::››

ፕ/ር መስፍን ‹‹አዳፍኔ›› በሚለው መጽሐፋቸው የኢትዮጵያን ያለፈ ታሪክ ታላቅነት ስለመጠበቅ፣ ለአቻ ምሁራን/ጓደኞቻቸው (አብዛኞቹ ከእርሳቸው ጎን ቆመው ለአገራቸው እና ለሕዝባቸው ሰላም እና ደህንነት በጋራ በአደባባይ ከመታገል ይልቅ በግል እያብጠለጠሉ የሚያሟቸው) ለመግለጽ አይደለም የፈለጉት:: ይልቁንም ‹‹የኢትዮጵያ ዓይን›› በመሆን ከኢትዮጵያ ተነጥሎ ላለውና ከአያቶቹ እና ከቅድመ አያቶቹ ታላቅነት ጋር ተለያይቶ ለሚገኘው ለአዲሱና ለአገር ተረካቢው ወጣት ትውልድ ለማመላከት ነው ጥረታቸው:: በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መስፍን በዳሳሹ ዓይናቸው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የት ላይ እንደነበሩ፣ አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ወይም ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በሚሠሩት ሥራ ምርጫ ላይ ተመሥርቶ ወደፊትስ የት ላይ እንደሚሆኑ እና እንደማይሆኑ በግልጽ የተመለከቱበትን ዘገባቸውን አቅርበዋል::

ይህ መጽሐፍ ታላቅ የነበረችው ኢትዮጵያ በአሁኑ ጊዜ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ እና በኢኮኖሚ ምስቅልቅ ሁኔታ ላይ የምትገኝ መሆኗን፣ የኢትዮጵያ የተሻሉ ቀኖች እየመጡ እና ከአድማስ ጫፍ ላይ እየታዩ መሆናቸውን ወዘተ. በሚመለከት የግል ሐሳባቸውን በውል እያስቀመጡ ጥልቀትና ስፋት ባለው ሁኔታ ትንታኔ የሰጡበት ታላቅ ሥራ ነው:: ‹‹አዳፍኔ›› በሚገባ የተሰናሰሉ ታሪካዊና የዘመኑ የፖለቲካ ትንታኔዎችን በማጣመር እንዲታዩ የተደረገበት፣ በርካታ ኢትዮጵያውያን የሞራል ግዴታቸውን ከመወጣት ይልቅ ከዳር ቆመው እየተመለከቱ አገሪቱ ወደከፋ አዘቅት ውስጥ እየተጋዘች ባለበት ሁኔታ ኢትዮጵያውያን ታላቅ ጥንቃቄ በተላበሰ መልኩ እንዴት አድርገው እራሳቸውን ከእራሳቸው መጠበቅና ማዳን እንደሚችሉ ለማሳየት ጥረት የተደረገበት ብሩህ መስተዋትም ነው::

የመጽሐፉ ርእስ በራሱ በርካታ የተወሳሰቡ ስሜቶችንና ትርጉሞችን አካትቶ የያዘ ነው:: ‹‹አዳፍኔ›› የሚለው ቃል በአንድ በኩል የመቅበር ሂደትን የሚያሳይ ወይም ደግሞ አንድን ነገር አፈር ውስጥ መደበቅን የሚያመላክት ሲሆን የእሳት መጥፋትንና የቀረውን ፍም በአፈር ወይም ደግሞ በውኃ ማጥፋትን ሊገልጽም ይችላል:: በሌላ መልኩ ይታይ ከተባለ ደግሞ ጥቂት ተግባራት ገና በመጀመሪያው የአፈጻጸም ደረጃቸው በድንገት የመክሰማቸውን ሁኔታ ሊያመላክት የሚችል ይሆናል:: በኢትዮጵያ የወታደራዊ ሥርዓት የቋንቋ አጠቃቀም ‹‹አዳፍኔ›› በተለምዶ ‹‹ባዙቃ›› እየተባለ የሚጠራው መሣሪያ ነው:: በአጠቃላይ ‹‹አዳፍኔ›› የሚለው ቃል አንድን ነገር ወይም ደግሞ ሂደትን የሚያፍን፣ የሚያንቅ፣ ትንፋሽ የሚያሳጣ፣ የሚያጠፋ፣ የሚከለክል እና የሚያደናቅፍ መሆኑን ይገልጻል::

‹‹አዳፍኔ›› የሚለው ቃል ድብቁ መልዕክት የበለጠ አሳማኝ ይመስለኛል:: (መስፍን አዳፍኔን በአሁኑ ጊዜ ላለው ለወጣቱ ትውልድ እና ለመጭው ትውልድ ማስታወሻ እንዲሆን በማሰብ የሰጡት ስያሜ ነው ብዬ አስባለሁ::) ወጣቱ ትውልድ ያለፉትን ትውልዶች ከባድ ድክመት በውል ተገንዝቦ የራሱን ኃላፊነት መወጣት እንዲችል የተሰጠ ማስጠንቀቂያ መሆኑን እገነዘባለሁ:: የኢትዮጵያ ውጣቶች የአዳፍኔን አስፈሪ ሁኔታ በውል አጢነው ያለፉት አባቶች፣ አያቶችና ቅድመ አያቶች የፈጸሟቸውን ስህተቶች በመድገም ራሳቸውን ከውሸት ተራራ ሥር ቀብረው እንዳይገኙ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል::

ፕ/ር መስፍን ለኢትዮጵያ ወጣቶች በሦስት መሠረታዊ ሐሳቦች ሊገለጽ የሚችል ታላቅ መልዕክት አላቸው ብዬ አስባለሁ:: እነርሱም:- አንደኛ፣ ከተወሰኑ ቡድኖች የራስን በራስ የማጥፋት አስከፊ አደጋ ኢትዮጵያን ሊታደጓት የሚችሉት የኢትዮጵያ ወጣቶች ብቻ ናቸው:: ሁለተኛ፣ ኢትዮጵያን ከጎሰኝነት እሳትና ከሃይማኖት ጽንፈኝነት ሊታደጓት የሚችሉት የኢትዮጵያ ወጣቶች ብቻ ናቸው:: ሦስተኛ፣ የማኅበረሰቡን የግንኙነት ክር ከበጠሱት የድሮዎቹና የአሁኖቹ ትውልዶች፣ አውዳሚ ከሆነው የፖለቲካ መዋቅር፣ ግራ ከተጋባው የኢኮኖሚ ሥርዓትና የሕዝቡን መንፈሳዊ ሕይወት ሊመለስ በማይችል መልኩ ካጠፋው ትውልድ ኢትዮጵያን ሊታደጓትና ሊያድኗት የሚችሉት ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ብቻ ናቸው የሚሉ ናቸው::

‹‹አዳፍኔ›› በአንድ ወቅት ምናልባትም በቅኝ አገዛዝ ዘመን የነበረ ሥር የሰደደ የአፍሪካ በሽታ ነው:: ‹‹አዳፍኔ›› አሕጉሪቱን ሙሉ በሙሉ በመበከል መልካም ምግባር፣ ዕውቀት፣ ታማኝነት ወዘተ. ያላቸው ሰዎችን እንዳታፈራ በማድረግ ምድረበዳ አድርጓታል:: ‹‹አዳፍኔ›› አሕጉሪቱን የጊንጥ ማጠራቀሚያ ቅርጫት አድርጓታል፤ አንድ ጊንጥ ከቅርጫቱ ውስጥ ለመውጣት ሙከራ በሚያደርግበት ጊዜ ሌሎቹ ጊንጦች ወደ ቅርጫቱ ውስጥ ስበው ያስቀሩታል:: ‹‹አዳፍኔ›› የአእምሮ በሽታ ነው:: የ‹‹አዳፍኔ›› በሽታ ሰለባዎች በዘላቂነት ፀረ ነጻነት፣ ፀረ እኩልነት፣ ፀረ ፍትሕና ፀረ እድገት ናቸው:: በሌላ አገላለጽ ለአዳፍኔ በሽታ ሰለባዎች ነጻነት ማለት የእነርሱ ነጻነት ብቻ ነው፤ እኩልነት ማለት የእነርሱ እኩልነት ማለት ብቻ ነው፤ ፍትሕ ማለት ለራሳቸው ብቻ ነው፤ ልማት ማለት በሚያስገርም ሁኔታ ብዙሃኑ ሕዝብ በረኀብ እየተሰቃየ ባለበት ሁኔታ እነርሱ ግን ከመሬትና ከሌላም ሀብት በርካታ ረብጣ ገንዘብ እያግበሰበሱ ወደ ኪስ ማጨቅ ማለት ነው::

‹‹አዳፍኔ›› የአምባገነናዊ የጭቆና አገዛዝ መለያ ባሕሪ ወይም መገለጫ ነው፤ ‹‹አዳፍኔ›› መሬቱን፣ ማዕድናቱንና ጌጣጌጡን ሁሉ ደብቆ ይይዛል፤ ሐይቆችንና ወንዞችን ሁሉ በራሱ ቁጥጥር ሥር ያደርጋል፤ አዳፍኔ አምላክ መሰል ሥልጣን አለው፤ የአዳፍኔ ምኞት ለሌላው ሕዝብ ትዕዛዝ ነው፤ አዳፍኔ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን በሽታ ነው::

‹‹አዳፍኔ›› በምን መልኩ ይገለጻል? (1ኛ) እውነትን በመጨቆንና በማጥፋት፣ (2ኛ) ትምህርትንና እውቀትን በመጨቆንና በማጥፋት፣ (3ኛ) እውነት ሊሰራጭበትና ሊስፋፋበት የሚችለውን ማናቸውንም ቀዳዳ ሁሉ በመዝጋት፣ (4ኛ) መንታ ምላስ ያላቸውን ቅጥፈትና ውሸት ሲገምዱ የሚውሉና የሚያድሩ ደናቁርት ካድሬዎችንና አስመሳዮች ሆድ አደሮችን በመቅጠር፣ እና (5ኛ) ሐሳቦችና ዕውቀቶች በሕዝብ መካከል እንዳይሰራጩ የሕትመት ውጤቶችን በሁሉም መንገዶች በመዝጋት ወዘተ. ይገልጻል::

‹‹አዳፍኔ›› ከኢትዮጵያና ከሕዝቧ ላይ

ወደ ገፅ 10 ዞሯል



## የዜጎች ድምጽ

(በዚህ ዐምድ ኢትዮጵያውያን የማኅበራዊ ድረ ገጽ ተጠቃሚዎችን የሚያወያዩና የሚያከራክሩ አንኳር ጉዳዮች ተመርጠው ይቀርባሉ)

አቻምየለህ ታምሩ

# ብአዴን የሕወሐት ነውረኛ ቡድን እንጂ የአማራ ሕዝብ አካል አይደለም!

## • ያልተኖረውን የብአዴን ዘመን ዳሰሳ

በክፍል አንድ ጽሑፌ እንደጠቆምኩት ሕወሓት ኢሕዴንን ኅብረ ብሔራዊ ድርጅት አድርጎ ከሐረርና፣ ከሲዳሞ፣ ከወለጋ፣ ከደብረ ዘይት፣ ከኮረም፣ ከኤርትራና ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች የተወጣጡ የኢሕአፓ ታጋዮችን በነአንበርብር አማካኝነት ከኢሕአፓ በማስኮብለል ነበር ያቋቋመው። ኢሕዴን ከ1973 እስከ 1985 ድረስ «የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ» ወይም በምህጻረ ቃል ኢሕዴን ተብሎ እየተጠራ ኅብረ ብሔራዊ ድርጅት ሆኖ «ሲታገል» እንደቆየም ይታወቃል። በ1985 ዓ.ም. ደግሞ የአማራን ውልክና ከመአሕድ ለመጫረትና መአሕድን ለመዋጥ ሕወሓት የብሔረሰብ ድርጅት አደረገው። በዚህ ምክንያት ዛሬ ብአዴን ለ35 ዓመታት የአማራን ሕዝብ ወክዬ ስለታገልኩ አማራው 35ኛ ዓመት ልደቴን ሊያከብርልኝ ይገባል እያለ ነው። በእውነቱ እንደዚህ ዓይነቱ ሰንፋጭ ድፍረት አይደለም ለአማራ ሕዝብ ይቅርና ለአልፎ ሂያጅም ይገለማል። ማንም እንደሚያውቀው ኢሕዴን ከ1985 ዓ.ም. በፊት ሕብረ ብሔራዊ ድርጅት ነበር፤ ብአዴን የሚል የሕወሓት አጃቢ የተፈጠረው በ1985 ዓ.ም. ነው። ታዲያ እንዴት ብሎ ነው የ23 ዓመቱ ብአዴን የ35ኛ ዓመት ልደቴን አክብሩልኝ እያለ ያለው? ሕብረ ብሔራዊው ኢሕዴን የአማራ ተወካይ ነበር ለማለት ነው? እንዴት ሊሆን ይችላል? የአማራ ሕዝብ ያልኖረውን ዘመኑን አክብርልኝ ሲለው ከዚህ በላይ መናቅ የለም ማለት መቻል አለበት።

የወያኔ ታማኝ ሞግዚት ሆኖ የኖረው ሳይበቃው ያልተኖረ ዘመኑን ሕዝቡ እንዲያከብርለት እያስገደደ ዛሬም ድረስ የቀጠለው ነውረኛው ብአዴን ላለፉት ሃያ አራት ዓመታ በኤርትራዊው መብራህቱ ገብረሕይወት (መብርህቱ በሚል ኤርትራውያን እናቱና አባቱ ባወጡለት ስም የሚታወቀው አንበርብር በሚል የበረሀ ስም የሚጠራውና በሚኒስትርነት ስሙ ደግሞ በረከት ስምኦን ተብሎ የሚታወቀው ግለሰብ እንደሆነ ልብ ይሏል) እየተዘወረ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ ሁኔታ አማራው ላይ ሕወሓት ባልተወለደ አንጀቱ ጫካ በነበረበት ጊዜ የቋጠረውን ቂምና ጥላቻ ሁሉ ያለ ርህራሄ እንዲያወራርድ ፈቅዷል።

ከመብራህቱ ገብረሕይወት የተምታቱ ታሪኮች ዋናው በዘሩ ኤርትራዊ ሆኖ ሳለ የአማራ ድርጅት መሪ መሆኑ ነው። ይኼ ከሞራል አንጻር ለአማራ ሕዝብ ስድብ ነው። መብራህቱ ገብረሕይወት በሕብረ ብሔራዊ ድርጅት ውስጥ ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚል ከሆነ ኢትዮጵያንም ቢመራ ጥያቄ ባልተነሳበት ነበር። ሰው አገሬ የሚለው አገሩ መሆኑ ይታመናልና። የዘር ፖለቲካ የሚያራምድ ግን የግድ እሱም ዘሩን የሚያቅፍ የፖለቲካ ድርጅት ወስጥ መግባት ይጠበቅበታል። ሕወሓት «አማራ በዘሩ መደራጀት አለበት» ብሎ ሲያበቃ፣ አማራውን ግን እንዲመሩ ያስቀመጣቸው አማራ ያልሆኑትንና ከልዩ ልዩ ዘሮች ያውጣጣቸውን ምንደኞችና አማራን በመጥላት ክብረ ወሰን የተቀዳጁ ቅጥረኛ ሰው በላዎችን በመሰብሰብ ነው።

አዲሱ ለገሠ፣ ህላዌ ዮሴፍ፣ ተፈራ ዋልዋ፣ ታደሰ ካሳ፣ ታምራት ላይኔ ወዘተ. እንደ መብራህቱ ገብረሕይወት ሁሉ አማራ ያልሆኑ ነገር ግን የአማራ ሕዝብ ወኪል እኔ ነኝ የሚሉ የአማራ

> ብአዴን ከተመሠረተ በኋላ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማራ መጥፋቱን በወያኔ ፓርላማ ሪፖርት መደረጉን ሁላችንም ሰምተናል። ለመሆኑ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማራ የት ጠፋ?

ሕዝብ ጠላቶች ናቸው። እነዚህ ሁሉ ሕወሓት ያበጃቸው ፍጡራን አማራውን በማዳከም ሕወሓትን ለማጠናከር በአማራ ሕዝብ አናት ላይ የተቀመጡ የአማራ ቀንደኛ ጠላቶች ናቸው። የወሎ መሬት ተቆርሶ ለትግራይ ሲሰጥ፤ የጎንደር መሬት ተገምሶ ለትግራይ ሲታደል፣ ጎጃም ለጉምዝ ተላልፎ ሲሰጥ፤ ሸዋ ለሁለት ሲከፈል፤ አማሮች እንደ በግ በኦነግና በሕወሓት ሲታረዱ እነመብራህቱ ገብረሕይወት፣ አዲሱ ለገሠና ታምራት ላይኔ የሰጡትን ምላሽ መቼም ልንረሳው አንችልም። አንድ ጊዜ ስለወልቃይትና ሑመራ እንዲሁም ሰሜን ወሎ ወደ ትግራይ መካለል ተጠይቆ አዲሱ ለገሠ ሲመልስ እወልከዋለሁ ከሚለው ከአማራ ወገን ሳይሆን ከትግራይ ወገን ሆኖ «የአማራው ገዢ መደብ ከትግራይ ቆርሶ የወሰዳቸው መሬቶች ስለነበሩ ነው ወደ ትግራይ የተካለሉት» ያለው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው። ዛሬ ፓስተር ሆኛለሁ እያለ የሚያጭበረብረው ታምራት ላይኔም አማሮች አርባጉጉ፣ ሐረር፣ ወለጋ፣ አርሲ ወዘተ. እንደ ፋሲካ ዶሮ ሲታረዱ ‹‹ከአማራ ክልል ውጭ ያለ አማራ አናውቅም›› ብሎ ተሳልቆባቸዋል።

በክፍል አንድ ከቀረበው በተጨማሪ ብአዴን የአማራ ሕዝብ ጠላትና የሕወሓት ሎሌ ስለመሆኑ በርካታ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል። ላለፉት ሃያ አራት ዓመታት ሕወሓት በአማራ ሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ግፍ የሚያንገበግባቸው አንዳንድ የድርጅቱ ወጣት ካድሬዎች ጉርፋርዳ እና ቤንሻንጉል አገራችሁ አይደለም ተብለው አማሮች ከኖሩበት ቀየ ተፈናቀለው ሜዳ ላይ የመውደቃቸው ድርጊት የእግር እሳት ሁኖ የሚለበልባቸው ብዙ ልጆች ነበሩ። በዚህ ሁኔታ ያዘኑና የተቆጡት ወጣቶቹ ‹‹ብአዴን የሚባለው ድርጅታችን ቆሜለታለው የሚለው ፍትሕ የት አለ፤ እኩልነትስ ከወዴት አለ? ኢትዮጵያስ የሁላችን አገር ነች የምትባለው መገለጫው ምንድ ነው?›› እያሉ የብአዴንን ሥራ አስፈጻሚ ሞግተዋል። ሆኖም ግን እነዚህ የሕዝብ ጥያቄዎች በአንዳንድ ህሊና ባላቸው የብአዴን ካድሬዎች መካከል መመላለስ ሲጀምሩ «ብአዴን ተዳክሟል» ተብሎ ግምገማ እንዲያካሂድ በሕወሓት ትዕዛዝ ተላልፎ ነበር። እነዓለምነው መኮንን «በባዶ እግርህ የምትሄድ ድሀ፣ ትምክተኛ ወዘተ.» ብሎ ሕዝቡ ላይ የተሳለቁበት በወጣት የብአዴን አባላት መካከል የሕዝቡ ችግር በመነሳቱ «ብአዴን ተዳክሟልና ግምገማ ያስፈልገዋል» ብሎ ሕወሓት ባዘዘው መሠረት በተጠራው ስብሰባ ላይ ነበር። ልብ በሉ እንግዲህ! የአማራ ጉዳይ በብአዴን ዘንድ የውይይት አጀንዳ ሆኖ ሲቀርብ በሕወሓት ዘንድ ብአዴን እንደተዳከመ ይቆጠራል። ከጅምሩ ብአዴን የተመሠረተው የአማራ ነስፍ አድን የሆነውን መአሕድን ለመዋጥ መሆኑን ከፍ ብለን ተነጋግረናል። ሕወሓት ብአዴንን ያበጀው የታገለለትን አማራን የማጥፋት ፕሮግራል እንዳሻው ለማስፈጸም እንቅፋት የሚሆንበትን ለአማራ የሚቆረቆር ድርጅት ውጦ ለማጥፋትና አማራን የማዳከም ፕሮግራሙን በአማራ ስም በስውርና በዘዴ የሚያስፈጽምለት ድርጅት ስላስፈለገው ነው። የብአዴን አፈጣጠር የሕወሓት ለምዱን አውልቀን እርቃኑ አስቀርተን ስናየው ዓላማው ይህ ነው።

ዛሬ መብራህቱ ገብረሕይወትና አዲሡ ነጻነትን ሳያውቁ ራሳቸውን የአማራ ነጻ አውጪ አድርገው ራሳቸውን ቢያቀርቡም እውነታው ግን ሁለቱም የሕወሓትን ዙፋን ከመጠበቅ የዘለለ ምንም ሚና የሌላቸው፤ ያልሆኑትን ለመሆን የሚውተረተሩ የአማራ ሕዝብ ገዳዮች ናቸው። ጀርባቸውን ጠንቅቆ ለሚያውቅ እነዚህ ግለሰቦች ስለ አማራ ሕዝብ ነጻነትና ክብር ይሠራሉ ብሎ ማሰብ የሚቻልበት ሁኔታ የለም። መብራህቱ ገብረሕይወትና አዲሱ ምንም እንኳ ሕወሓት ለዓላማው ያስቀመጣቸው ፈዳያኖች ቢሆኑም የአማራ ሕዝብ እያኖራቸው ለአማራ ሕዝብ ግን ፍቅር የሌላቸው፤ ከአማራ ሕዝብ መሪ ነን እያሉ የማይመሩ፤ ዕለት ዕለት በሚፈጥሩት የፍርሃት አረንቋ ውስጥ የሚኖሩ፤ ሠላም የራቃቸውና ወያኔ የአማራን ሕዝብ ለማረድ የሳላቸው ካራዎች ናቸው። በመሆኑም አማራው ከእነዚህ ግለሰቦች እውነትን ፈልጎ ማግኘት፤ ነጻነትን ጠይቆ መቀዳጀት፤ ለፍትሕ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አይችልም። የአማራ ሕዝብ ከጉራፋርዳ እንዲወጣ የተደረገበት ምክንያት ምንድ ነው ተብለው ሲጠየቁ «የትምክህተኞች ጥያቄ» ብለው ይሳደባሉ። አያቶቻችን በደምና አጥንታቸው ያቆዩልንን ድንበር አፍርሳችሁ ለባእዳን ለምን ትሰጣላችሁ ሲባሉ የጦርነት ናፋቂ ጥያቄ እያሉ ይዘባበታሉ። እንደምን ሁኖ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማራ ከቁጥሩ ጎድሎ ተገኘ ሲባሉ የነፍጠኞች ወሬ እያሉ ይሳለቃሉ። አዎን እነመብራህቱ ገብረሕይወት የሚፈልጉት አማሮች ስድባቸውን ተሸከመው ተዋርደው እንዲጠፉ እንጂ እውነትን፤ ፍትሕንና እኩልነትን እንዲጠይቁ አይደለም።

የብአዴን ተልኮ በአማራ ልጆች መካከል የፍትሕ፤ የነጻነትና የእኩልነት ጥያቄዎች ሥር እየሰደዱ ሲመጡ ጠያቂዎችን የአማራ ልጆች መግደልና ማሰር በየዕለቱ የምንሰማው «የልማት» ዜናችን ሆኗል። በአማራ ሕዝብ መካከል እንደ እሳት ሰደደ እየተሰራጩ ላሉ የህልውና፣ የፍትሕ፤ የነጻነትና የእኩልነት እጦት ጥያቄዎች ከሕወሓት መራሹ ሞግዚት (የተቋቋሙት ለነዚህ ሕዝባዊ ዓላማዎች ስላልሆነ) መልስ ማግኘት የሚቻል አይደለም። ለዚህ ውለታው ነው እንግዲህ የነመብርህቱ ድርጅት ሰሞኑን «የአማራን ሕዝብ ነጻ ላወጣ የተመሠረትኩበትን ሠላሳ አምስተኛ የልደት ቀኔን ላከብር ነው» እያለ የአማራን ሕዝብ የሚሳደበው። በእውነቱ ይህ ቡድን ነጻነትን ሳያውቅና ለነጻነት ሳይመሠረት ነጻ አወጧኂችሁ ማለትን ብቻ የሚያውቅ፤ ወያኔ በእንደራሴነት ለሰጠው ሕግ እንኳ መገዛትን ሳይወድ ስለ ሕገ መንግሥት የበላይነት የሚሰብክ፤ ራሱን ከሁሉ በላይ እኔ ነኝ ብሎ ሲያበቃ ስለ እኩልነት ለመስበክ የማያቅማማ የነውረኞች ስብሰብ ነው። መብራህቱ ገብረሕይወትና አዲሡም የዚህ ነውረኛ ቡድን አካል እንጂ የአማራ ሕዝብ አካል እንዳልሆኑ በአማራ ሕዝብ ላይ የፈጸሙትን ጥፋት በዝርዝር ገልጫለሁ።

ብአዴን ከተመሠረተ በኋላ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማራ መጥፋቱን በወያኔ ፓርላማ ሪፖርት መደረጉን ሁላችንም ሰምተናል። ለመሆኑ ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማራ የት ጠፋ? በአገሪቷ ካሉ ብሔረሰቦች መካከል እንደምን ሁኖ የአማራ ቁጥር ብቻ ሊቀንስ ቻለ? ከአማራ ክልል ወጥተው በሌላ ክልል የሚኖሩ አማሮች ይሄ አገራችሁ አይደለም፤ ወደ አገራችሁ ሂዱ ተብለው እየተባረሩ ባሉበት ሁኔታ ሦስት ሚሊዮን አማራ ወዴት ሄደ? ኢትዮጵያ አገራቸው ካልሆነች የአማሮች አገር ወደየት አለች? ከጉራፈርዳ እና ከቤንሻንጉል ተነቅለው ሜዳ ላይ እንዲወድቁ የተደረጉ አማሮች ▶


# ኮከብ ብርሃን
## የባህል ሕክምና ማዕከል

ማንኛውም ባለጉዳይ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በትህትና በማስተናገድ ላይ ሲሆኑ በአሁኑ ሰዓት ትክክለኛ ፈውስ የተገኘላቸው በሽታዎች በከፊል:-

- ለሆድ ሕመም
- ለእጅና ለእግር ቁርጥማት
- ለአስም
- ለሾተላይ
- ለራስ ሕመም
- ለእግር ፈንገስ
- ለሚጥል በሽታ
- ለማዲያት
- እጁን ለሚጠባ
- ለትምህርት
- ለእጅ ሰብእ
- ለጭርት ወይም ማሳከክ
- ለአይነ ጥላ
- ለወር አበባ መብዛት
- ሌሊት ለሚሸና

በተለይ የብዙ ሰዎችን ችግር የሆነውን የስንፈተ ወሲብ /በመቀባት/ ብቻ ፈውስ ይሰጣል።

አድራሻ:-

ሐና ማርያም ቀለበት መንገድ ንግድ ባንክ ፊት ለፊት

ለበለጠ መረጃ:- 0911 808241 /0913 778746/ 0912 635069

በእውነት ስለ እውነት እንተጋለን!!

በአበራ ለማ - ከኖርዌይ



▶ በደላቸው ምንድን ነው? ለነዚህ ጥያቄዎች አማራ ካልሆንን ሞተን እንገኛለን የሚሉት መብራህቱ ገብረሕይወትና አዲሱ ለገሠ መልስ አይሰጡም።

ብአዴንን ሕወሓት ከፈጠረ ጀምሮ በአማራ ሕዝብ ላይ የደረሰው ሥነ ልቦናዊ ግፍ ተነግሮ አያልቅም። የአማራን ቅስም መስበር፤ ትምክህቱን ማስተንፈስ፤ ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ማዋረድ፤ ወዘተ የሚሉት በወያኔ የተሰጣቸው የነመብራህቱ ገብረሕይወትና አጋሮቹ ዋነኛው ፀረ አማራ መፈክሮቻቸው ናቸው። በነዚህ መፈክሮች መሪነት ከሦስት ሚሊዮን በላይ አማሮች ጠፍተዋል፤ ኢትዮጵያ አገራችሁ አይደለችም ተብለው ከወለጋ፣ ከአርሲ፣ ከጉራፈርዳ፣ ከቤንሻንጉል ወዘተ. ውጡ ተብለው ሜዳ ላይ ተጥለዋል። ከንግዱ አምባም ሳይቀር ቀስ በቀስ አማሮች እንዲጠፉ ተደርገው ሥፍራቸውን ለወያኔዎች እንዲለቁ ሁነዋል። ከፐ/ር አሥራት ጀምሮ ለአማራ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምልክትና ጥሩ ምሳሌ የሆኑ አማሮች ቀስ በቀስ እንዲጠፉ መደረጋቸውን በዓይናችን ዓይተን በጆሯችን ሰምተናል። ብአዴን የተባለው ድርጅት በአማራ ስም ቢቋቋምም ቅሉ ዋና ተግባሩ ግን አማሮችን ማዋረድና አማሮች ላይ የሚደርስባቸውን በደል ሊታደጉ የሚችሉ የአማራ ልጆችም እንዳይኖሩ ማጥፋት ነው።

ከሁለት ዓመት በፊት የአማራ ሕዝብ «ትምክህተኞች» እያለ የሚያስጨርሰው መብራህቱ ገብረሕይወት አያሌው ጎበዜን አስነስቶ ገዱ አንዳርጋቸው እንዲተካው አድርጓል። በእርግጥ የአያሌው መሄድና የገዱ መምጣት ለአማራ ሕዝብ ነጻነትና ክብር የሚፈይደው አንዳችም ቁም ነገር የለም። አያሌውም ሆነ ገዱ ለሕዝብ ይቅርና ለራሳቸውም ክብር የሌላቸው ደካማ ሎሌዎች መሆናቸው የታወቀ ነው። ለራሱ ክብር ያለው የሕዝብ ወኪል እወክለዋለው የሚለው ሕዝብ ከኖረበት ቀየ እየተነቀለ ሜዳ ላይ ሲጣል አይቶ ዝምታን አይመርጥም። ዓለምነው መኮንንና ገዱ ከአማራ ሕዝብ አብራክ ወጥተው ደሃውን አማራ በሙሉ ነፍጠኛ፤ ትምክህተኛ፤ እብሪተኛ ሌላም ሌላም እያሉ እያዋረዱ፤ እየሰደቡ ለሳዳቢ አሳላፊው የሰጡ የወያኔ አሽከሮች ናቸው። ለአማራ ሕዝብ የአያሌው በገዱ «መተካት» የተዋረደውን የአማራ ሕዝብ ክብር አይመልሰውም፤ ሕዝቡ ያጣውን ነጻነት መልሶ አያቀዳጀውም። ለሱዳን ተቆርሶ የተሰጠውን በአያቶቻችን ደምና አጥንት የቆየውን መሬት አያስመልሰውም። የወልቃይት ሕዝብ የደም እንባ እያነባ ለትግራይ በግዳጅ የተሰጠውን ለም መሬት አያስመልሰውም። ታዲያ ስለምኑ ነው የአማራ ሕዝብ የሕወሓት/ብአዴንን ልደት የሚያከብረው? በረኀብ ሲያልቅ ወያኔ ስለደበቀለት? አማራው ክብሩና ታሪኩ ስለተዋረደ? ለየትኛው ውለታው ነው የአማራ ሕዝብ የብአዴንን ልደት የሚያከብረው? የብአዴን ልደት ከአማራ ሕዝብ ጋር ምን ያገናኘዋል? ምንም!

‹‹አዲስ ገጽ›› መጽሔት

በቅርብ ቀን ይጠብቋት!

መጽሔቷ፣ በሀገርና በዓለም አቀፍ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ይበልጥ ትኩረት ታደርጋለች። በተጨማሪም፡-


- ኪነ-ጥበባዊ መዝናኛዎችን
- ታሪክና ባህልን
- ሥነ-ልቦናንና ፍልስፍናን
- ህግ ነክ ጉዳዮችን …ወዘተ


ትዳስሳለች።

‹‹አዲስ ገጽ››፣ አስተማሪና አዝናኝ ሀሳቦች የሚስተናገድባት የሕዝብ ገጽ።

በተለያዩ የነጻ ፕሬስ ውጤቶች ላይ ለዓመታት በሰሩ ጋዜጠኞች የምትዘጋጅ መጽሔት!

# "የኤርትራ ምሽት" ለስደተኞች ደራስያን





ካንድ አስርት ዓመታት በላይ አባል ሁኜ የቆየሁበት ኖርዌጂያን ፔን (Norsk PEN/ Norwegian PEN) የሚያከናውናቸው የተላያዩ ተግባራት አሉት። ከነዚህም አበይት ትግባራቱ መካከል በያገራቱ ያሉ እህት ማህበራትን መታደግና ለስደተኛ ደራስያን የከተሞች የጥገኝነት (By Forfather) መብትን ማሰጠት ነው። ሥራቸውም እንዲታተምና ለሕዝብ እንዲደርስ ጥረት ያደርጋል። በእስር ላይ የሚገኙ የሌሎች አገር ደራስያንንና ጋዜጠኞችን ማሰቢያ ምሽቶችን በየጊዜው ያዘጋጃል። ከዚህ ቀደም የማሰቢያ ምሽት ከተዘጋጁላቸው ጸሐፍት መካከል እውቁ ጸሐፊ ኢትዮጵያዊው እስክንድር ነጋና ስዊድናዊ/ ኤርትራዊው ዳዊት ይስሃቅ ይገኙባቸዋል። እናም ኖርዌጂያን ፔን ባለፈው ሐሙስ ጥቅምት 25 ቀን "የኤርትራ ምሽት" የተሰኘ የምሽት ፕሮግራም አዘጋጅቶ ነበር። ይህ ምሽት ኤርትራ ወስጥ ያለውን የሰብአዊ መብት ጥሰትና አጠቃላይ ስቃይ ሸሽተው የወጡ የኤርትራ ደራስያንን ለመታደግ ነበር። ደሳለ በረከትና ኃይሌ ቢዘን አብርሃ የተባሉት የኖርዌይ ከተሞች ጥገኛ ደራሲያንና ናታን ሐዲሽ ሞገስ የተባለው የፖለቲካ ስደተኛ ደራሲ የምሽቱ ተጋባዥ ዝግጅት አቅራቢ ደራስያን ነበሩ።

ኃይሌ ቢዘን አብርሃ የምሽቱ ሌላው ኮከብ ደራሲ ነበር። ይህ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ከፍተኛ ትምህርቱን ተከታትሎ የነበረ ደራሲ ከራሴ ሥራዎች ጀምሮ የኢትዮጵያን ሥነ ጽሁፍ እያጣጣመ ያደገ የሥነ ጽሑፍ ሰው እንደሆን በግል አጫውቶኛል። ኃይሌ በኖርዌይ አገር ሕጻናት ጣፋጭ ነገሮችን በመብላት፣ ጥርሶቻቸው እንዳይጎዱ የሚማሩበትን የተረታ ተረት መጽሐፍ ወደ ትግርኛ ቋንቋ ተርጉሞ አሳትሞ አቅርቧል። ይህ "ካርዩስና ባክቱስ .... KARIUS og BAKTUS " የተሰኘ ተረታ ተረት በጨዋታ አስመስሎ ልጆች የጥርሶቻቸውን ጤንነት እንዲጠብቁ በበርቱ የሚመክር በመሆኑ፣ ወላጆችና ሕጻናት በእጅጉ ይወዱታል። ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ከመተርጎሙም በላይ አዝናኝ ፊልሞች ተሠርተውበታል። ኃይሌ ውብ በሆነ ድራማዊ አቀራረብ በኦቨር ሄድ ፕሮጀክተር እየታገዘ፤ ሥራውን በትግርኛ ቋንቋ አስደምጧል።

ሌለው የምሽቱ ኮከብ ኤርትራዊ ደራሲ ወጣቱ ናታን ሐዱሽ ሞገስ ነበር። ናታን በኖርዌይ የስደተኞች ካምፕ በነበረበት ወቅት የታዘበውን የሕይወት ልምዱንና ብዙ ብዙ ገጠመኞቹን በመጀመሪያ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥፎ፤ ባሜሪካን አገር ለሕትመት ያበቃ ጀግና ነው። ናታን አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተወልዶ ያደገና አምቼ በሚባለው ቡድን ውስጥ ተጠርዞ ወደ ኤርትራ ተባሮ የነበረ ብሩህ አእምሮ ያለው ወጣት ነው። "MOTTAKET (የስደተኞች ካምፕ እንዲሉ በኖርዌይ ቋንቋ)" በሚል ርእስ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጽፎት የነበረው ይህ መጽሐፉ፣ ወደ ኖርዌጂያን ቋንቋ ተተርጉሞ ቀርቧል። ናታን በእንግሊዝኛ ከታተመው ከዚህ መጽሀፉ ላይ ጥቂት ገጾችን በንባብ አሰምቷል - በምሽቱ። ጥሩ የኖርዌጂያን ቋንቋ ተናጋሪ የሆነው ይህ ወጣት ወደፊት በርካታ ሥራዎችን በሚችላቸው ቋንቋዎች ሁሉ ያቀርባል የሚል ተስፋ በብዙዎቻችን ዘንድ አሳድሯል።

ባንድ አገርኛ ተረት ላይ የተመሰረተ ሥእላዊና በኖርዌጂያንኛ ቋንቋ የተዘጋጀ ሥራውን በኦቨር ሄድ ፕሮጀክተርና ባንዲት ኖርዌጂያዊት አንባቢ እየተረዳ አቅርቧል። ስለኖርዌይ አኗኗር ገጠመኞቹም ጣእም ባለው ለዛ በእንግሊዝኛና በትግርኛ አቅርቧል። መቀመጫው ባሜሪካን አገር ስለሆነው ስደተኛው "ፔን ኤርትራ" እንቅስቃሴም ገለጻ አድርጓል።

በዚህ ምሽት ላይ ቀርቦ ከነበሩ ሌሎች ዝግጅቶች መካከል የታሪክ ተመራማሪዋና በትሮምሶ ዩኒቨርስቲ የሰላም ጥናት ማእከል ኃላፊ የሆነችው ክርስቲነ እስሚዝ ሲሞንሰን የኖረዌይንና የኤርትራነ ገንኚነት በሚመለከት ያቀረበችው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። እሷ እንደምትለው ታዋቂው የኖርዌይ ቤተክርስቲያን እርዳታ ደርጅት (NORSK KIRKE HJELP/ NORWEGIAN CHURCH AID) በትግሉ ዘመን መጀመሪያ ከጀብሃ ጋር ከዚያም ከሻቢያ ጋር በምስጢር አብሮ የግንጠላው ሥራ እፍጻሜ ላይ እንዲደርስ እንዴት ብርቱ አገልግሎት እንደሰጠ ነው።

ይህ ድርጅት መቀመጫውን ሱዳን ላይ አድረጎ፤ በእርዳታ ሰጪ ደርጅት ሽፋን ተገንጣዮችን እስከመጨረሻው ደርስ በገንዘብና በቁሳቁስ ሲረዳ እንደነበረ ክርስቲነ በሰፊው አብራርታለች። ታዲይ የሚያስደንቀው ነገር በእርዳታ ደርጅት ሽፋና ባንዲት አገር የሉዓላዊነት ጉዳይ ላይ እንዲህ ያለ መርዘኛ ነገር ድርጅቱ መፈጸሙ ብቻ ሳይሆን፤ በኋላ የተከሰተው ጉድ ጭምር ነው። አቶ አሳይያስ የእርዳታ ድርጅቶች ስውር ድጋፍ አግኚ ስለነበርና ከነጻነት በኋላ አብረውት ቢሰነብቱ ለሱም ጤና እንደማይሰጡት በመረዳቱ ሁሎችነም ከኤርትራ ምድር ሲያባርር፤ አብሮት የቀረው በቸኛው ደርጅት ይህ የኖርዌይ የቤተክርስቲያን እርዳታ ደርጅት ብቻ ነበር። ውሎ አድሮ ግን ለዚህ ደርጅትም የሚራራ አንጀት ሊኖረው አልቻለም። እንደትናንቱ ሁሉ የኖርዌይ ቤተክርስቲያን እርዳታ ደርጅት የሌሎች ተቃዋሚዎቹ ስውር አጋር ሊሆን ይችላል በሚል ፍራቻ አባሮታል። ይህ በምሽቱ ብዙዎቻችንን ያስገረመም ያሳዘነም ዜና ነበር። በኖርዌጂያን ቋንቋ የተጻፈው የጥናት ጽሑፍዋ ማጣቆሚያ የሚከተለው ነው።

ደራሲ እስጢፋኖስ ገብረ ሚካኤል ከኔ ጋራ

በእለቱ መድረክ ተሰጥቶት ያልነበረ ሌላ አውቅ ኤርትራዊ ደራሲና ያቶ ኢሳይያስ ክፉ አስተዳደር ተቃዋሚ የሆነ ደራሲ በምሽቱ አግኝቻለሁ። ይህ ሰው የታሪክና የረዥም ልቦለድ ደራሲው እስጢፋኖስ ገብረ ሚካኤል ነው። የሥራዎቹን ናሙናዎች ይዞ ከታዳሚዎች ጋር ተገኝቷል።

ከዚህ ቀደም እ.አ.አ. በ2010 ዓ.ም. የኖርዌይ ደራስያን ማሕበር ለአሥመራው ያቶ ኢሳይስ እስረኛ ደራሲና ጋዜጠኛ ዳዊት ይስሃቅ "ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ ሽልማት" መሸለሙ ይታወሳል። እነዚህ ዛሬ በኖርዌይ የከተሞች ጥገኝነት ያገኙ ደራስያን፤ ዳዊት ይስሃቅና ሌሎችም ከእስር ይፈቱ ዘንድ ዓለም አቀፍ ትጋላቸውን እንደሚቀጥሉ አስታውቀዋል።

በነገራችን ላይ ዓለም አቀፉ ፔን የተቋቋመው እ.አ.አ. በ1921 ዓ.ም. በእንግሊዛዊው ጸሀፊ በጆን ጋልስዎርዚ አማካኝነት ሲሆን፤ P.E.N. ማለትም ትርጉሙ የገጣሚያን፣ የወግ ጸሐፊዎች ያለያም የአርታኢያንና የልቦለድ ደራስያን «Poets, Essayists and Novelists» ወይም «Poets, Editors and Novelists» ዓለም አቀፍ ማህበር ማለት ነው። የኖርዌይ ፔን ደሞ የዓለም አቀፉ ፔን በተቋቋመ ባመቱ በ1922 ዓ.ም. እውቅናን ያገኘ ነው። Stavanger, Kristiansand, Oslo, Trondheim, Molde, Skien, Drøbak, Lillehammer, Bergen og Tromsø የተባሉት የኖርዌይ ከተሞች ከተለያ አገሮች ለሰደዱ ደራስያንና ጥገኝነት የሰጡ ከተሞች ናቸው። የኖርዌይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በፔን ኖርዌይ አማካኝነት ለያንዳንዱ የከተማ ጥገኛ ስደተኛ ደራሲ ባመት የ100000.00 ሺ.ህ ክሮነር ድጎማ ይሰጣል። 48 የከተማ ጥገኛ ስደተኛ ደራስያን በ14 የኖርዌይ ከተሞች ውስጥ ሲኖሩ፤ ከነዚህ ደራስያን መካከል አንድ ኢትዮጵያዊ ይገኝበታል።

## ቀን መቁጠሪያ ለማኝ!

ዓለማየሁ ከበደ

ወርልድ ባንክ አይ-ኤም- ኤፍ- እየቀለደብኝ
የጣሊያን አይጦች እየቦጫጨቁኝ
አሜሪካ እንግሊዝ እያላገጡብኝ
ጀርመን የዘር ጥናት እያካሄደብኝ
በችጋር ቢያልቁብኝ ጥማድ በሬዎቼ
በውሃ ጥም ቢያልቁ በጎች ፍየሎቼ
ወንድሜን እህቴን አባት እናቶቼን
ከተማ ገብቼ እዳልሞት ልማጸን
በገዛ አገሬ ይህን ሁሉ ችየ ለምኜ በኖርኩኝ
ልመና ወጥሮኝ እራሴም ሳላውቀው ካሌንደር ተባልኩኝ
በኔ የሚለምኑት የአገሬ መሪዎች
ፍርፋሪ በሊታ ሆዳሞች ካድሪዎች
ቀን መቁጠር ያልቻሉ ከታሪክ ጀምረው
በኔ መለመኛ ሲንበላጠጡባት ሲታዩባት ከብረው
ተመስገን አምላኬ የልማቱ ጮራ በኔም አለፈብኝ
ዕልልልልልል! በለማኝ አገሬ ካሌደር ተባልኩኝ
በእኔ ተለምኖ እኔም ለማኝ ሆኜ
መለመኛ አገሬ ብትደፈርብኝ ግንባር ቀደም ሆኜ።
የክብር ሞት ለመሞት በትውልድ አገሬ
መንገድ ላይ የማጥር ፈርሶ ቤት ትዳሬ
የቆሰለ ለማኝ የሌለኝ አድራሻ
ከመነሻ ተፈናቃይ የጠፋኝ መድረሻ
ታዲያ ካሌንደር መሆኔን እኔ እንኳ ሳላውቀው
የገዛ ወንድሜ ኢትዮጵያዊ ወገኔ መስታዎቴ አወቀው
ቁጥር ብቻ ሆኜ ወረቀት የያዘው
በእኔ ተለጥፎ ሰው ብቻ የሚያነበው
ለሰው ቀን መቁጠሪያ አስታዋሽ ከሆንኩኝ
የኔን ቀን ሳላውቀው የኔ ሰው ካወቀኝ
ጠቃሚም ከሆንኩኝ እንደቀን መቁጠሪያ
እኔ አላፊ ሆኜ ማሳለፊያ ማኩሪያ
የአገሬ መሪዎች እግዜር ይባርካችሁ
ካሌንደርም ሆኜ ካገለገልኳችሁ

# ኢትዮጵያውያንን ከራሳቸው መጠበቅ . . .

የማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ሕይወትን በመጭመቅ እኩይ ምግባር ላይ ተጠምዶ ይገኛል። አዳፍኔ በኢትዮጵያ የተስፋ፣ የእምነት፣ የልግስና፣ የፍላጎት መነሳሳት፣ የቃል ኪዳን፣ የክብር፣ የታማኝነት፣ የሞራል ልዕልና፣ የመልካም ፈቃድ ማውደሚያ እኩይ ምግባር መሣሪያ ሆኖ ይገኛል። አዳፍኔ በዕውቀት ሊወገድ ይችላል፤ ዕውቀትና ትምህርት የአዳፍኔ ጠላቶች ናቸው፤ አዳፍኔም የዕውቀትና የትምህርት ጠላት ነው።

አዳፍኔ ተጽዕኖው በወጣቶች ላይ የጠነከረ ነው። እነዚህ ወጣቶች አያትና ቅድመ አያቶቻቸው በሠሯቸው ስኬታማ ሥራዎች ላይ ኩራት እንዲሰማቸው ከማድረግ ይልቅ በአባቶቻቸውና በእናቶቻቸው ላይ ስለደረሰው ስቃይ እንዲጸጸቱ ይገደዳሉ። በኢትዮጵያዊነታቸው ራሳቸውን እንዲያንኙ ከማድረቅ ይልቅ ወጣቶች በጠባብ ጎሰኝነትና በሃይማኖት ጽንፈኝነት ላይ እንዲንጠላጠሉ ይገደዳሉ። ወጣቶች መብቶቻቸውን እንዳይጠቀሙ ኃይል እንዲያጡና አቅመቢስ እንዲሆኑ፣ ድምጻቸው እንዳይሰማና በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያጡ ይሆናሉ።

የአዳፍኔ ውልደት ግዙፍ የሆነ የሥርዓት መውደቅንና በማኅበረሰብ ደረጃ መዋቅራዊ ውድቀትን ያስከትላል። ያንን የህልውና ውድቀት (መክሸፍ) ነው መስፍን ወልደማርያም ኢትዮጵያውያንን እንደ ኢትዮጵያውያን በመጽሐፋቸው ለማሳየት ጥረት ያደረጉት። የፕ/ር መስፍን የመክሸፍ ትንታኔ በርካታ መገለጫዎች አሉት። አንድ የማኅበረሰብ ፕሮጀክት የአፈጻጸም ብቃት ሳይኖረውና ከፍጻሜ ሳይደርስ ሲቀር ወይም ደግሞ ለማኅበረሰቡ ፍሬ ሳያፈራ ሲቀር ‹‹መክሸፍ›› ሊከተል ይችላል። አንድ ሰው ዓላማውን ሳያሳካ ሲቀርና እድገት ማስመዝገብ ሳይችል ሲቀር መክሸፍ ይመጣል። በጋራ ልማትና ማኅበራዊ ለውጥ ማምጣት ሳይቻል ሲቀር መክሸፍ ይከተላል።

ፕ/ር መስፍን ለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውን መክሸፍ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶችን እንደሚከተለው ግልጽ አድርገው አቅርበዋል። አንደኛ፣ የአስተዳደር ሥርዓቱ በሕግ የበላይነት ቁጥጥር ሥር መዋል ሲሳነው። የዚህ መክሸፍ ውጤት ጨቋኝ አገዛዝን ያለምንም ችግር መቀበል ወይም ደግሞ በእግር በመወሰን ወደ ስደት መንጎድ ይሆናል። ሁለተኛ፣ የኢትዮጵያ ምሁራን መክሸፍ። ምሁራንና የልሂቃኑ ክፍል በማንኛውም ጊዜ ለሚመጡና ሥልጣንን በሕዝብ ድምጽ ሳይሆን በመሣሪያ ኃይል ለሚቆጣጠሩ አምባገነኖች ራሳቸውን (ስብዕናቸውን) ይሸጣሉ። በእያንዳንዱ የአገዛዝ ዘመን ምሁራን የትኛውንም ዓይነት እኩይ ድርጊት አልሰማሁም፣ አላየሁምና ምንም ዓይነት ነገር አልተናገርኩም በማለት ከኃላፊነት ይሸሻሉ። ምሁራን በአጠቃላይ የተማረው ኅብረተሰብ ክፍል ሕዝቡን አስተባብረው በመምራቱ ረገድ ሳይሳካላቸው ቀርቶ ከሽፈዋል፤ እንዲሁም በሥልጣን ላይ ያለው አካል ወንጀልና

የተሳሳቱ ሥራዎች ሲሠራ በሚገባ መዝግበው በመያዝ ለመጭው ትውልድ ለማስተላለፍ ምንም ዓይነት እርምጃ ስለማይወስዱ ከሽፈዋል። ከሁሉ የከፋው ደግሞ የራሳቸውን ስህተቶች እንደገና ለማባዛት በሚመስል መልኩ ያለፈውን ትውልድ ስህተት እንደ ትክክለኛ ነገር ለመጭው ትውልድ ሌት ቀን እንደበቀቀን እየደጋገሙ መንዛታቸው ነው።

የሃይማኖት መሪዎችም መንፈሳዊ አመራር መስጠት ባለመቻላቸውና ከእነሱ የሚጠበቀውን ሁሉ ማድረግ ባለመቻላቸው ከሽፈዋል። ከሁሉም በላይ ልብን የሚሰብረው እውነታ ደግሞ፣ በአሁኑ ጊዜ በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተንጠልጥለው የሚገኙት የደናቁርት ስብስብ የአካዳሚ የትምህርት

ማስረጃዎችን ከዲፕሎማ መቀፍቀፊያ የኢንተርኔት ወፍጮዎች በሕዝብ ገንዘብ እየገዙ ልክበር እያሉ የማስቸገራቸው ጉዳይ ነው። ሥልጣናቸውን ለማሳመርና ማስዋቢያ ነገሮችን በመቀባባት በሥልጣን ላይ ያሉት ስብስቦች ባለሥልጣን መሳይ አካል የፈረመበት ማሕተሞችን በመጠቀምና የሸፍጥ የምስክር ወረቀቶችን በመግዛት ዶ/ር፣ ፕ/ር፣ የመንግሥት አማካሪና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተወካዮች በማለት ራሳቸውን በመጥራት የአስመሳይነት ሥራቸውን በመተግበር ላይ ይገኛሉ።

በእኔ አመለካከት የደናቁርት ስብስቦቹ ያልተረዱት ነገር ቢኖር አንድ አህጽሮተ ቃል የተጻፈበት ብጣሽ የተጭበረበረ የዲፕሎማ ወረቀት አንድን ሰው ታላቅ መሪ ሊያደርገው እንደማይችል በውል ያለመገንዘባቸው ጉዳይ ነው። በአንድን ሰው ታላቅ የሚያደርገው ርዕዩ፣ አእምሮውና አስተሳሰቡ ነው እንጅ በስርቆት የተገዛ ዲፕሎማ አይደለም።

ሦስተኛ፣ ለኢትዮጵያውያን አርአያ ሊሆናቸው የሚችል አካል ያለመኖሩ ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ስኬታማ የሆኑ አገሮች ባለመኖራቸው ምክንያት ኢትዮጵያውያን ስለተሻለ አመራርና ኅብረተሰብ ለመማርና ለማወቅ አልቻሉም።

‹‹አዳፍኔ›› በኢትዮጵያ ሰፊ መሠረት ባለው ታሪካዊና ማኅበረ ፖለቲካዊ ከባቢ ላይ የተዋቀረ ነው። መጽሐፉ የአገራችን ህልውና ተጠብቆ እንዲዘልቅ የሚያግዙ ወሳኝ ወሳኝ ነጥቦችን ግልጽ አድርጓል።

# ‹‹በዓለም ታሪክም ያለመስዋዕትነት . . .

መብታቸው ነው። እኛ ግን በመስዋዕትነት ከዚህ እንደደረስን ወደፊትም የሚከፈለውን ከፍለን በሰላማዊ ትግሉ ነው የምንቀጥለው። ትግላችን መሣሪያ ከታጠቀ ገዳይ ሥርዓት ጋር እንደሆነ ይገባናል፤ እየሞትንም ሁላችን እስከምናልቅ ድረስ አጠናክረን መቀጠላችን ግን ግድ ነው። ዋናው ሳናቋርጥ ተራራውን ለመውጣት የምናደረገው ጥረት ነው። ይህ እስከ ቀጠለ ድረስ ሕዝባችንን ነጻ ማውጣታችን የማይቀር ነው። የሌሎችን የትግል ሥልት እኛ አንነካም፤ መብታቸው ነው። እኛ የመንሳትም የመስጠትም መብት የለንም፤ የእኛ መብት ግን የመረጥነውን ሰላማዊ ትግል ይዘን መቀጠል ጋር ነው።

ሥርዓቱ ምርጫ ቦርድን መሣሪያ በማድረግ ፓርቲዎችን ሲሠራ ሲያፈርስ የሚጎዳው አገዛዙ እንጅ እኛ አይደለንም። ይህ ድርጊት እንደሆነ ግልጽ ነው ግለሰቦችን የሰላማዊ ትግል አብቅቷል እንዲሉ ያስገደዳቸው። አገዛዙ ይህን ሕገ ወጥነቱን እስካላቆመ ድረስ ብዙ ወገኖች የሰላማዊ ትግልን አዋጭ ያለመሆን እሳቤ ሊያዳብሩ ይችላሉ። ይህ ከማንም በላይ የሚጎዳው አገዛዙን ነው። የምርጫ ቦርድ በፍሃትም ይሁን በተገዥነት የሚወስናቸው ውሳኔዎች ለሌላ ግብዓት ይሆናሉ እንጅ እኛን የሚጎዳን ነገር የለም። እኔና የትግል አጋሮቼ ይህን ሁሉ አፋኝነትና ሕገ ወጥነት ሁሉ ተቋቁመን በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ ሰላማዊ ትግሉን መቀጠላችን እሙን ነው። በ1984 ዓ.ም. የፖለቲካ ትግል ስጀምር ይህ ሁሉ እንደሚሆን አምኘበት የገባሁት ነገር ስለሆነ አሁንም ሐሳቤን የሚያስቀይረኝ ነገር አይኖርም። የእኛን ሰላማዊ ትግል ሊያስቀምን የሚችል ሕዝብ ብቻ ነው። ሕዝባችን እስካሁን ላደረጋችሁት ትግል እናመሰግናለን፤ ከዚህ በኋላ ግን የታገላችሁለት ዓላማ ግብ ስለመታ አታስፈልጉንም

ሲለን ብቻ ነው ትግል የምናቆም። ሰላማዊ ትግል ከማንኛው ትግል የበለጠ ዋጋ ቢያስከፍልም የሚመጣው ውጤትም የዛኑ ያክል ጣፋጭ ነው። በጠመንጃ የሚመጣ ለውጥ የሰለማዊ ትግል ያክል ዴሞክራሲያዊ ባህል የለውም። ወያኔ በጠመንጃ ሥርዓት ቀየረ ግን ምን ይዞ መጣ? ዴሞክራሲ? ሰላም? የሕግ የበላይነት? ምንም አላመጣም። ፈረንጆችን ለማስደሰት ሕገ መንግሥት አረቀቀ እንጅ ሕገ መንግሥቱን እኮ የሚንደው ራሱ ወያኔ ነው። ከጠመንጃ አፈሙዝ ውስጥ ዴሞክራሲም፣ የሕግ የበላይነትም፣ ልማትም የለም፤ ያለው አፋኝነትና አምባገነናዊነት ብቻ ነው።

የሚገርምህ ሰለማዊ ትግሉ አዋጭ አይደለም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች የሚያነሱት ‹‹ይኸው ወያኔ ቢሮችሁን ዘጋባችሁ! እስኪ እናንተ ምን ተጠቀማችሁ? ሁልጊዜ ስትታሰሩ ነው የምናያችሁ›› የሚሉ ነገሮችን ነው። ግን እንደዚህ የሚሉ ወገኖች ከእኛ ጋር ቢጨመሩ ኖሮ ድምጻችን የበለጠ ይሰማ ነበር። የነጻነት ቀን ቶሎ እንዲመጣ ተማርን የሚለው ወገን ወደ ፖለቲካው መግባት አለበት። መታሰሩ መገደሉ የትግሉ አካል እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። ኔልሰን ማንዴላ እኮ 27 ዓመት ታስሮ ነው ደቡብ አፍሪካን ነጻ ያወጣት። መታሰር፣ መገደል፣ መሳደድ ባይኖር፣ ሥርዓቱ አፋኝ ባይሆን እኮ ትግልም አስፈላጊ አልነበረም። ወደ ትግል የገባነውም እነዚህን ነገሮች ለማስቀረት ነው።

<u>በቅርቡ ወደ አሜሪካን አገር ሊያደርጉት የነበረውን ጉዞ ኢምባሲው ቪዛ በመከልከሉ ምክንያት እንደተስተጓጎለ ተገልጿል። ወደ አሜሪካን አገር የሚሄዱት ለምን ነበር? የአሜሪካ ኢምባሲስ በምንም ምክንያት ነው ቪዛ የከለከለዎት?</u>

ወደ አሜሪካ የምሄደው በአሜሪካና በአውሮፓ ያለው የመኢአድ ድጋፍ ሰጭ ኮሚቴ ባደረገልኝ ጥሪ መሠረት በአሜሪካ የተለያዩ ግዛቶችና አውሮፓ ተንቀሳቅሼ መኢአድን ለማጠናከርና ድጋፍ ለማሰባሰብ ነው የምሄደው። መርሐ-ግብሩ ለሦስት ወራት የሚቆይ ነው። ይሁን እንጂ እንደተጠቀሰው ኢምባሲው ቪዛ ከልክሎኛል። ኢምባሲው ቪዛ የከለከለበት ምክንያትም በጣም የሚያሳዝን ሆኖ ነው ያገኘሁት። ‹‹ሀብት፣ ልጅ፣ ሚስት የለህም›› በማለት ነው ቪዛ የከለከለኝ። እኔ የፖለቲካ ታጋይ እንጅ ነጋዴ ስላልሆንኩ መኪናና ቤት ሊኖረኝ አይችልም። አብዛኛውን ልሠራ የምችልበትንም ዕድሜዬን ያሳለፍኩት በፖለቲካ ትግል ላይና በእስር ቤት በመሆኑ እነርሱ የተጠቀሱትን ነገሮች ማፍራት አልችልም፤ አልቻልኩምም። ለነገሩ ዝም ብለው ነው እንጅ ሚስትና ልጅም አሜሪካን አገር ለመሄድ ዋስትና ሊሆኑ አይችሉም። በእስር ረጅም ዕድሜ የኖረና የተረጋጋ ሕይወት እንዳይመራ የተደረገ ሰው እንዴት ቤተሰብ ሊመሠርትና ንብረት ሊያፈራ ይችላል? በእውነቱ ኢምባሲውን ራሱን ትዝብት ውስጥ የሚከት ነገር ነው የተፈጸመው።

እኔ አሜሪካን አገር የምሄደው እዚያው ለመቅረት እንዳልሆነ ግልጽ ነው። አሜሪካን አገር የመሄድ ዕቅድ ቢኖረኝ ኖሮ 24 ዓመታት መታገል አይጠበቅብኝም ነበር። ድህረ ምርጫ 97 ከእስር ስንፈታ ለሁላችንም (የቅንጅት አመራሮች) ኢምባሲው ቪዛ ውሰዱ ብሎን እንደነበርም አይዘነጋም። እንዲያውም ከሁለት ዓመት የነጻ ሕክምና ጋር ሁሉ ነበር የፈቀደልን። አሜሪካ የመኖር ዕቅድ ቢኖረኝ ኖሮ ያኔ መሄድ እችል ነበር። የእኔ ዓላማ የጀመርነውን የፖለቲካ ትግል እንዴት እናጠናክረው፣ እንዴት እናስቀጥለው የሚለው ነው።

# የሕወሓት/ኢሕአዴግ . . .

የሩቁን ትተን የቅርባችንን የትናንትናውን የ2007 ዓ.ም. ምርጫ ብንመለከት እንኳን ሕወሓት/ ኢሕአዴግ ሥልጣን ላይ ለመቆየት ከአንድ ዓመት ቀድም ብሎ ጥርጊያ ተጀምሮ ነበር። ካቴናዎች ሥራ እንዲበዛባቸው ተደርጓል፤ ጋዜጠኞች ብዕራቸውን ተነጥቀው ግማሾቹ ግዞት ያመለጡት ስደትን መድረሻቸው አድርገዋል፤ አንድነትን የመሰሉ ከብርቱ ትግልና ውጣ ውረድ በኋላ የመንግሥት ቅርጽ ለመያዝ የቻሉ ፓርቲዎች በተባበረ ክንድ በግፍ ተመትተው እንዲጠፉ ተደርገዋል፤ የፖለቲካ አመራሮች ወደ እስር ቤት ተልከዋል ወዘተረፈ። (በነገራችን ላይ ስለ አንድነት ሳስብ ሬዲዮ ፋናና ኢቲቪ ከየስርቻው ተለቃቅመው ለመጡና መርህ ሳይጣስ መርህ ተጣሰ ሲሉ ለነበሩ፤ የእውነተኛውን አመራር ሥም ለማጉደፍ የተሰጣቸው ሰፊ ሽፋን ነው። ይኸው ትልቁ አንድነት በችሮታ የተሰጠው ‹‹ተቃዋሚ›› የሚል ስም የለበሰ ቡድን ሥራውን የጀመረው የአንድነትን ታፔላ ከተከለበት በመንቀል ነው። ቀበና አካባቢ በትልቁ ይታይ የነበረው ታፔላ አሁን የለም። ፓርቲውም በሕይወት የለም። አንቀላፍቷል። እናም ከምርጫው በፊት አንድነት እንዳይዳከም ፈልጌ ነው ሲል የነበረው የምርጫ ቦርድ፣ ኢቲቪና ፋና ዋርካውን አንድነት ገዝግዘው የጣሉበት መንገድ ይደንቀኛል።)

‹‹በነገራችን ላይ›› ብዬ ረጅም ሄድኩኝ። እና ምን ለማለት ፈልጌ ነው፣ አንደኛው የኢሕአዴግ መልክ ሥልጣን ለመልቀቅም ሆነ ለማጋራት የማያስብ፣ ምንም ዓይነት ርምጃ ያለ ምንም ርህራሄ ለመውሰድ የቆረጠ ነው። ይኸኛው ለአገራችን ከፍተኛው አደጋም ነው። ዳግም ጦርነትና የጦርነት ወሬ እንድንሰማ ያደረገን ይኸኛው መልከ ጥፉ መልኩ ነው። አስተዋይና አርቆ አሳቢ የሆኑ ፖለቲከኞች ጨዋታውን ርግፍ አድርገው ትተው ወደግል ጉዳያቸው እንዲገቡ ያደረጋቸው ይሄው ነው። ምክንያቱም ጨዋታው ውስጥ ከገቡ በደንብ መጫወት ነው። ከተጋጠሙም በደንብ መጋጠም ነው። ጨዋታው የውሸት እንደሆነ እያወቁ ወደ ጨዋታ መግባት (ኢሕአዴግ የሚፈልገው ይህን ነው) በሕዝብ ላይ ግምኛ መቀለድ ነው። በተለመደው መንገድ ከምርጫ በኋላ እስከ አራት ዓመት ድረስ የአድማቂነት ጨዋታ በአምስተኛው ዓመት ላይ ደግሞ የጨዋታው ፈርስ አካሄድ ፈጽሞ ጠቃሚ አይደለም።


ሁለተኛው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መልክ ከምርጫ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት የሚይዘው መልኩ ነው። ይህ ሥርዓት ሥልጣን መያዙን ካረጋገጠ በኋላ በአንጻሩ ለዘብተኛ ለመሆን ይሞክራል። ለምሳሌ የ2007 ዓ.ም. ምርጫን መቶ በመቶ (አሳፋሪ በሆነ ሁኔታ) ከወሰደ በኋላ ካሰራቸው ብዙ ጋዜጠኞች ውስጥ የተወሰኑትን ፈትቷል። ጋዜጠኝነት መበረታታት አለበት እያለ ነው። ሙስናና የመልካም አስተዳደር ችግር ላይ ሰይፍ መዘዣለሁ አጨብጭቡ እየተባለም ነው። ይህ እንግዲህ የሁለተኛው መልኩ መገለጫ ነው። መልካም መምሰል ግን መልካም አለመሆን።

ሲቀረፍ አላዬንም እንጅ ስለ ሙስና፣ የፍትሕ መዛነፍ፣ ስለ የመልካም አስተዳደር ችግር ያልሰማንበት ጊዜ የለም። ኢሕአዴግ በእንቁላሉ ጊዜ መቅጣት ካልቻለ በኋላ አይችልም። አባልጎ እንደገና የመቅጣት ምፀት ይሉታል። አብዛኛው ለማለት በሚያስደፍር መልኩ አባላቱ የሚሰበሰቡት ለጥቅም ነው። በኢሕአዴግ መታወቂያቸው ሳይቀር ያስፈራሩበታል። ሕዝብን እንዲያገለግሉ በተሰጣቸው ማዕረግ ይዘርፉበታል። ጋሽ ኃይለማርያም አልሰሙ እንዳይሆን እንጅ ‹‹ለምን ከኢሕአዴግ ጋር ጠጋ ብለህ አትበላም?›› የሚለው የተለመደ ምክር ነው።

ስለዚህ ኢሕአዴግ በሁለተኛ መልኩ ሕዝቡን ለይስሙላ ለማስደሰት ከሰበሰባቸው መርህ የለሽ የማይታረቁ ካድሬዎች ጋር ትግል እንደጀመረ ያስመስላል። ኪራይ ሰብሳቢ የሚለው ስያሜ ከተቃዋሚዎች ወደእነርሱ ይዞራል። እነርሱም ያውቁታል። ይህ ማበል የምርጫ ወሬ ሲመጣ ይቆማል። ለሁሉም አበል ይቆረጣል፤ ከፍያ ይሰጣል።

ዘውድና ጎፈር ጨዋታው አሰልቺም አድካሚም ነው። ዞሮ ዞሮ ግን ባለሁለት መልክ መሆን ቀጥፎ የሚበላው ራሱን ኢሕአዴግን ነው። እስከዚያው ድረስም አገርንም ሕዝብንም እየበላ ይቆያል። ለአንድ ወጥ ለሆነ አቋም መታገል ግን መታደል ነው።

## ታሪክና ኅብረተሰብ



ታዬዎስ ታንቱ
(የስልክ ቁጥር:- 0934996138 ፣ የመ.ሳ. ቁጥር:- 43414)

# ደካማ ሕዝብ የገዢዎች ፈረስ ነው ! !

ኢትዮጵያ አገራችን ከባቢሎን፣ ከፐርሺያና ከተቀሩት ጥንታውያን አገሮች ጋር በአሮጌው ዓለም ታሪክ ትታወቃለች:: ይህች አገር በብርቱ ትውልድ ዘመናት መልክዓ ምድራዊ ክልሏ እየሰፋ ደካማ ትውልድ ሲተካ ደግሞ እየጠበበ እስከ ዘመናችን ደርሷል:: አገሪቱ ለዘመናት በዘውድ ሥርዓት አስተዳደር ሥር ቆይታለች:: በዚህ ሂደት እስከ ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት ድረስ በባህላዊ አስተዳደር እንደኖረች ታውቋል:: ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ የዘመናዊ አስተዳደር ሐሳብን አፈለቁ:: ዘመናዊ የታሪክ ወሰነ ዘመንም ከእሳቸው አስተዳደር መነሻ ይጀምራል:: ዳግማዊ አጼ ቴዎድሮስ የዘመናዊ አስተዳደር ሐሳብን አፍልቀው ዘሩት:: ዳግማዊ አጼ ምኒልክ ውኃ እያጠጡ ኮትኩተው አሳደጉት:: ለፍሬም አበቁት::

ሰው በአገር ላይ ይወለዳል:: ሰው በአገር ላይ ይኖራል:: በአገር ላይ ይሞታል:: ትውልድ ይሞታል:: ትውልድ ይኖራል:: ትውልድ ያልፋል:: ትውልድ ይመጣል:: የሻሪ ሽረት ሕግ ይሠራል:: ትውልድ ሲያልፍ ትውልድ ይተካል:: ቋሚ ነገር የለም፤ ያልፋል፤ ያሳልፋልም:: ትውልድ ይቀጥላል፤ ይቀጥላል:: ዑደት ሒደት ነውና:: ትውልድም ጅረት ነው:: ይህ እውነት ነው:: እውነትም ይህ ነው:: በሁኔታዎች የሚወሰን እውነት አይደለም:: ዘላቂ እውነት ነው:: የማይለወጥ እውነት ነው:: ትውልድ ጅረት ነው::

ይህች ጥንታዊት አገራችን ዛሬ ለብዙሃን ገሃነም ሆናለች:: በእቶን እሳት ላይ ተቀምጠናል:: ነደናል፤ ተስፋ ቢስ ሆነናል:: የተስፋ ጭላንጭል አጥተናል:: ነገ ከዛሬ ይብሳል:: ጭንቀት ላይ ወድቀናል:: ቀጥሎ ምን ይመጣ ይሆን? የመልካም ኑሮ ብሩህ ተስፋ አይታየንም:: ጠላት በብረት ይገዛናል:: አመንምኖናል:: ብርታት ያንሳል:: ድክመት ይጥላል:: በድክመታችን ምክንያት አበሳችን በዝቷል:: አሁንም ተኝተናል:: ጥንታዊ አገር አለን:: ተከታታይ ታሪክ አስመዝግበናል:: ለም መሬት ይዘናል:: የሥራ ኃይል ሞልቶናል:: ወንዞችና ማዕድናት አሉን:: በቀን አንዴ ጠግበን ለመብላት ግን ተቸግረናል:: የመከራ ቀንበር ተሸክመናል:: በጭንቀት የሰመጠ ሥነ ልቦና ይዘናል:: በድክመታችን አበሳችን ጨምሯል::

ዛሬ ኢትዮጵያ ለብዙሃኑ ለደሃው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለከበርቴዎችም የጭንቅ ቀጠና መሆኗ ይስተዋላል:: ዛሬ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥትና በደርግ ወታደራዊ አስተዳደር በአንጻራዊ መልኩ በኅብረተሰባችን መካከል ይታይ የነበረው ውስጣዊ መረጋጋት የለም:: በኢትዮጵያ ውስጥ የትም ቦታ የተረጋጋ ሕይወት የለም:: ጭንቀት ነግሷል::

ገዢዎቻችን ከጭንቀታችን እንደሚያተርፉ ግን ብዙዎቻችን አናውቅም:: ስለ እውነት በእውነት እንናገር:: ይህን የምንገነዘብ በጣም ጥቂት ብቻ ልንሆን እንችላለን:: ብዙዎቻችን ለዚህ የሚያበቃ አስተዋይነት የለንም:: ድክመታችን የጨመረ ይመስላል:: አቅማችን እየወረደ መጥቷል:: በዚህ መነሻ ገዢዎቻችን በሥነ ልቦና የበላይነትን ሊጨብጡ በቅተዋል:: ብዙዎቻችን በእርግጥ ገዢዎቻችን በወታደራዊ መልክ የበላይነትን አግኝተው የኢትዮጵያን ሕዝብ ሥልጣን ሊቀሙ እንደቻሉ እናውቃለን:: ከዚህ ባነሰ አስተዋይነት ከተገደብን በሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሯችን እንኳን ሰዎች መሆናችን ያጠያይቃል:: ያም ሆነ ይህ ገዢዎቻችን የሥን ልቦና የበላይነትን ባይቀዳጁ ኖሮ የባርነት ዕድሜያችን ይህን ያክል ባልተራዘመም ነበር:: ግልጽ ነው:: የሥነ ልቦና ሽንፈታችን ከወታደራዊ ጥቃት በላይ ጎድቶናል:: በሥነ ልቦናው የተፈታ ሕዝብ የጦር መሣሪያ ሳይይዝ ከውጊያ ወረዳ የገባ ወታደር ነው:: ማንም ይጫዎትበታል:: ማንም ይነደዋል:: ማንም ያሽረክረዋል:: ትልቁ የጦር መሣሪያ የሥነ ልቦና ትጥቅ መሆኑን የምንናገረውም በዚሁ መነሻ ነው:: በውጊያ መስክም ቢሆን በሥነ ልቦናው የተረታ ሠራዊት እንደተማረከ ወታደር ይቆጠራል:: ምክንያቱም ፈጠነም ዘገዬ ጦርነቱ መበላሸቱ አይቀርምና ነው:: ቀጥሎ ምን ሊሆን ይችላል? ድል አድራጊው ወገን በአልቦ መስዋዕትነት ምርኮኛ ይሰበስባል::

ዛሬ ገዢዎቻችን ከመከራችን በማትረፍ ላይ ናቸው:: ከስሜት ተነስተን ሐሳባችንን የምናነብ አይደለንም:: ከተከታታይና ጥልቅ ምልከታ መነሳታችን ይታወቅ:: በዚህ ሒደት የሕዝቡ ጭንቀት ለገዢዎቻችን የሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያ ፍቱን እንክብል ሆኗል:: ጭንቅ ላይ ያለ ሕዝብ የመብቱን የአድማስ ስፋት ለይቶ አያውቅምና:: መብት ምን እንደሆነ ለመገንዘብ እንኳን በአስተውሎት ድህነት ይገደባል:: የአእምሮ ድህነት ከቁሳዊ ሀብት ማጣት የበለጠ እንደሚጎዳ ደግሞ በውል ይታወቃል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን ይጨነቃል? ለምን አበሳው በዛ? የኢትዮጵያ ሕዝብ አስታዋይ በሥነ መንግሥት በሥነ ቁጠባና በማኅበራዊ ሕይወት እሳቤ የጎለመሰ ሥነ ልቦና የታጠቀ ቢሆን ኖሮ ሁለንተናዊ መልካችን አሁን ካለንበትም በላይ ሊያስጨንቀን በተገባ ነበር:: ነገር ግን በዚህ ደረጃ የለንም:: በአለፉት ሃያ አራት ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያዊ ኩራታችንን አውልቀን በመጣል የገዢዎቻችን ዓላማ ማስፈጸሚያ ተንቀሳቃሽ መሣሪያ ሆነናል:: በዚህ ምክንያት ብዙዎቻችን መጪው ትውልድ ስማችንን በክብር እንዲያነሳ ለሚያደረግ ታሪካዊ ፋይዳ ላለው ብሔራዊ ጉዳይ ፈጽሞ አንጨነቅም:: ይልቁንም በተናጠል እያንዳንዳችን ለግል መናኛ ዕለታዊ ጥቅም እንጨነቃለን:: አርቆ አስተዋይነትን ያጣነው በእርግጥ ከግላችን በሰረጸ ድክመት ነው:: ሆኖም ከቀድሞ ዘመን አንስቶ የአንድነታችን የሉዓላዊነታችንና በአጠቃላይም የሕልውናችን ጠላት የሆኑት የዛሬዎቹ ገዢዎቻችን ትልቁን የአገር ጉዳይ ትተን እለታዊ ጥቅም ብቻ የምናሳድድ የወረደ ስብእና ያለን ደካማ ዜጎች እንድንሆን ከበረሀ ዘመን ሕይወታቸው አንስቶ በትጋት ሠርተዋል:: በዚህ ሒደት በተለይ በዕድሜያቸው ወጣት የሆኑ ዜጎች የኢትዮጵያን ሕዝብ ለሺህዎች ዓመታት አንድ አድርገው ያኖሩ በባህላዊና ሥነ ልቦናዊ ውርሶች እንዲያጣ ለማድረግ በአካል በጠበደሉ ነገር ግን በመንፈስ በመሰከኑ የአገዛዙ ካድሬዎች የተፈጸመው አፍራሽ ተግባር በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: በዚህ መነሻ ዛሬ በኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት የታነጸ በራሱ የሚተማመን መንፈሰ ጠንካራ ወጣት እያጣን ነው:: ይልቁንም ለገዢዎቻችን በሎሌነት አድሮ የእለት ጉርሱን ብቻ ለማገኘት የሚቋምጥ መንፈሰ ልፍስፍ ወጣቶች በዝተዋል:: ወይም ደግሞ በመንገድ ላይ የአገዛዙ ታጣቂ ትኩር ብሎ ስለተመለከተው ብቻ ሲጨነቅም አድሮ በነጋታው ወደ ስደት የሚያቀና ወጣት ብዙ ነው:: ብዙዎቻችን የትግል መንፈስ የለንም:: የመስዋትእነ አቋም የለንም:: የጭንቀት መንፈስ ነው ያለን:: ጭንቀት ደግሞ የፍርሓት ምልክት ነው:: ደካማነት ነው:: ገዢዎቻችን ኢትዮጵያን እናታችንን ትተን ነገዳችንን ወይም ጎሳችንን እንድናስብ ሲነግሩን ሳናመዛዝን በመቀበላችን ዛሬ ለምንገኝበት የጭንቀት ሕይወት ተዳርገናል::

በመሠረቱ የሕዝብ ጀግና የለውም:: አንድ ሕዝብ እንደወረደ ጀግና እንዲሆን የሚያደርግ ሰዋዊ ተፈጥሮም የለውም:: የአንድ አገር ሕዝብን እንዳለ ጀግና እንዲሆን መጠበቅ በሕዝቡ መካከል በትውልዶች ቅብብሎሽ ምንግዜም የማይጠፉትን ፈሪዎችን፣ ሰነፎችን፣ አታላዮችንና መሠሪዎችን መካድ ይሆናል:: መሆን ደግሞ የለበትም:: በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ጀግና እንዲሆን አይጠበቅበትም:: በዓለም ታሪክ ላይም ይህ ዓይነት ክስተት አልተስተዋለም:: ሕዝብ ለጀግች አጋር እንዲሆን ብቻ ይጠበቅበታልና:: ይህ መታወቅ አለበት:: ጀግና ታዲያ እንዴት ይፈጠራል? እንዴት ይቀረጻል? ጀግናን አንገብጋቢና ወቅታዊ ሥነ መንግሥታዊ ጉዳዮች ይፈጥሩታል:: እርግጥ ነው የጀግንነት መሠረታዊ ጽንሰ ሐሳብ ከወታደራዊ ተልእኮ ጋር ይሄዳል:: ይሄን አላጣንም:: ሆኖም የትኛውም ወታደራዊ የተግባር እንቅስቃሴ መነሻው ሥነ መንግሥት ነው:: በሥነ መንግሥት እሳቤ በሠላማዊ መንገድ ሊፈታ ያልቻለ ጉዳይ ወደ ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ያድጋል:: ይህ በአጽንኦት የሚሰመርበት ጉዳይ ይሆናል::

> ገዥዎቻችን ዘወትር ለድክመት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ። አንድን ግለሰብ ለሹመት ለማጨት እንኳን ከደካማ ጎኑ ይነሳሉ። ፈጽሞ ጠንካራ ጎን ተንደርድረው አያውቁም። ምክንያቱም ሁልጊዜም ሎሌ ይፈልጋሉና

ያም ሆነ ይህ አሁን ባለው አቋሙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነቱ፣ ለመብና ለክብሩ ለቆሙ ጀግኖች አጋር አይደለም:: ባለፉት ሃያ አራት አመታትም ውስጥ ይህ በተደጋጋሚ ተስተውሏል:: ለጀግኖች በአጋርነት የማይቆም ሕዝብ ደግሞ ዓላማ የለውም:: የሕይወት መርሕ የለውም:: የሕይወት ፍልስፍና የለውም:: ለእለት ጉርሱ ብቻ ይጨነቃል:: ለእለት ጉርሱ ብቻ የሚጨነቅ ሕዝብ ደግሞ የትውልድ አደራን ከፍጻሜ አይጨነቅም:: ይህ የደካማ ሕዝብ ባህሪ ነው::

ኢትዮጵያ አገራችን ብዙ ሕዝብ አላት:: ነገር ግን ሁለንተናዊ ሕዝባዊ ውጤቱ የሚያበረታታ አይደለም:: ይልቁንም በተቃራኒው የሚያሳፍር ነው:: ለክብሩ የቆሙ ጀግኖች በጠራራ ፀሀይ በአገዛዙ ታጣቂዎች ሲገደሉ የአጸፋ እርምጃ ለመውሰድ ቀርቶ ለተቃውሞ ሰልፍ እንኳን የማይወጣ ደካማ ሕዝብ ነው:: ደካሞች ነን:: ለመኖር ሳይሆን ለመብላት የምንኖር ከሆንን መቸም ምንጊዜም ከባርነት አንወጣም:: አስር የሥርዓተ አገዛዙ ታጣቂዎች አስር ሽህ ሕዝብን በአቢዮቱ አደባባይ እያጋደሙ እንደ ኳስ ሲለጉት እያየን ዝም የምንል ከሆንን ከተቀረው የዓለም ሕዝብ ጋር እኩል መሆናችንን ለመናገር እንዴት የሞራል ብቃት ሊኖረን ይችላል?

ብርቱ ሕዝብ ታሪክ ይሰራል:: ደካማ ሕዝብ ግን አያት ቅድመ አያቶቹ ያወረሱትን የታሪክ ውጤት በክብር ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ እንኳን አቅም ያጣል:: የአቅም ውስንነት ደግሞ መነሻው ራስ ወዳድነት ነው:: ራሱን ብቻ የሚወድ ሕዝብ ለአገር እንደማይበጅ በታሪክ ብዙ ጊዜ ታይቷል:: ራሱን ብቻ የሚወድ ግለሰብም ሥለተፈጠረ ብቻ የሚኖር አላስፈላጊ ዜጋ ብቻ ሆኖ ይቀራል:: ሕዝብም ሆነ ግለሰብ ለአገር እድገት መኖር ይጠበቅበታል:: ለመጪው ትውልድ አንድ አይነት አስተዋጽኦ አበርክቶ ማለፍ አለበትና:: ዛሬ ገዢዎቻችን በንቀት ይመለከቱናል:: እብሪታቸው አሻቅቧል:: እነሱ ሲያልፉ ልጆቻቸው እንዲገዙን ሁኔታዎችን ሲያመቻቹም ተስተውለዋል:: ልባችን ገምተዋላ!!

ዛሬ የመከራ ቀንበር ተሸክመን ዋይታ ስናሰማ ይስተዋላል:: ይህ ደግሞ የደካማ ሕዝብ ባሕሪ ነው:: የአገራችን ጉዳይ ሁሉ እንደሚያገባን ለምን አንረዳም? ለተናጠል ሕይወታችን ከምንጨነቀው ሩብ ያህሉን እንኳን ለአገራችን ለምን አናስብላትም? በድክመታችን መከራችን እየጨመረ ይሄዳል:: በስንፍናችን ጠላቶቻችን ይበረታሉ:: ምን እንደምንጠበቅ አይገባንም:: ነገ ሁላችንም እንደምናልፍ ይታወቃል:: ምንም ሳንሠራ ማለፉችን የማይቆጨን ከሆነ ግን በሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሯችን ችግር አለ ማለት ነው:: ገዢዎቻችን አርሶ አደሩን አፈናቅለው መሬቱን ራሳቸው ሲቀራመቱ ማናችንም አልደረስንላቸውም:: ተሰብስበን አቋም ለመውሰድ እንኳ አልደፈርንም:: በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ኢትዮጵያውያን ይገደላሉ:: ልብ ያለን ሰዎች ብንሆን ኖሮ በዚህም ጉዳይ ላይ ጥያቄ አንስተን አገዛዙን እናስጨንቅ ነበር:: ነገር ግን ይህንም አላደረግነውም:: ፈሪዎች ነን:: ደካሞች ነን:: ድንጋይ ወርውረው ፎቅ የሚያፈልቁ ገዢዎቻችን ዝንታለም የባዕዳን መሣሪያ በመሆን ኢትዮጵያን እናታችንን ሲያደማ ከኖረ ቡድን ብቻ በርካታ ጀኔራሎችን በአንድ ጀምበር በኢትዮጵያ ሕዝብ ገንዘብ ሲሾሙ መቼ ጠየቅን? ካዴት ኮርስ ያልገቡ በእጩ መኮንንነት ሒደት ያላለፉ በዘር ሐረጋቸው ብቻ ማእረግ ሲለብሱ ትንሽ እንኳን አልቆረቆረንም:: ምንም የማናውቅ የአብርሃም በጎች ነን ማለት ነው? የጄኔራሎችን አስቀደምን እንጅ የመሥመራዊና የከፍተኛ መኮነኖች ከመነሻው በዘር ሐረጋቸው ማዕረግ እንደታደላቸው በወቅቱ ሰምተናል::

መቼ ይሄ ብቻ! ወገኖቻችን በአያት ቅድመ አያቶቻቸው የሕይወት መስዋዕትነት ተጠብቆ ከኖረው መሬት ላይ በዘረኞች ቀጭን ትዕዛዝ ተፈናቅለው በየመንገዱ ወድቀው ስናይ የሰብአዊነት አቋም ወስደን በማበረታት የሞራል ስንቅ እንኳን ልንሰጣቸው ያልቻልን ጨካኞች ነን:: እያንዳንዳችን በእያንዳንዳችን ላይ መከራ ሲደርስ እንባችን ይቀድማል:: ከብስጭታችን ብዛት የተነሳ ችግራችንን በቃላት እንኳን አስተካክለን ለመናገር ያቅተናል:: ታዲያ በወገናችን ላይ በደረሰበት መከራ የምንመረቅነው ለምንድን ነው? ክፋት አንዱ የድክመታችን መገለጫ ነው:: የሁላችንም ጠላት ገዢዎቻችን ናቸው:: ክፋታችን ባሪያ አድርጎ አስገዛን እንጅ አልጠቀመንም:: አበሳችን ደግሞ በድክመታችን ልክ እየጨመረ ይሄዳል:: ለመከታችን መለኪያ ሚዛኑ ድክመታችን ነው:: ገዥዎቻችን ከመነሻውም በድክመታችን ገብተዋል:: ዙፋን ላይ መተኮፈሱ በኋላም ድክመታችንን መሠረት አድርገው ይጫወቱብናል:: ገዥዎቻችን ዘወትር ለድክመት ከፍተኛ ዋጋ ይሰጣሉ:: አንድን ግለሰብ ለሹመት ለማጨት እንኳን ከደካማ ጎኑ ይነሳሉ:: ፈጽሞ ጠንካራ ጎን ተንደርድረው አያውቁም:: ምክንያቱም ሁልጊዜም ሎሌ ይፈልጋሉና:: ዕውቀት ያለው ባለሙያ ሳይሆን ሁልጊዜ በሎሌነት የሚያገለግል ይሻሉና::

አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በጣም ብዙ ይቀረናል:: ንቃተ ሕሊናችን ሕሊናችን አልጎለመሰም:: ንቃተ ሕሊናችን ማጎልመስ አለብን:: ለገዥዎቻችን ልንታዘዝ አይገባም:: የነጻነት ጥያቄ ማንሳት ይጠበቅብናል:: ኢትዮጵያ አገራችን የገዢዎቻችን ብቻ ለምን ሆነች? ገዢዎቻችን ገንዘብ እንጅ ዜጎችን አይፈልጉም? በዜጎች ስቃይ ይደሰታሉ:: በዜጎች መከራ ይፈነድቃሉ:: ከበረሐ ሕይወታቸው አንስቶ በዘረፋ ኖረዋል:: እስከ መቼ በድክመታችን ይገዙናል? አስተዋይና ቆራጥ ዜጎች ሆነን መገኘት አለብን:: ኩሩ ኢትዮጵያውያን ሆነን መውጣት አለብን:: ገዢዎቻችን ከድንቁርና፣ ከረኀብ፣ ከበሽታና ከመሳሰሉት ነገሮች ሁሉ የከፋ ጠላቶቻችን ናቸው:: ድክመታችንን እናስተካክል:: የአገራችን ጉዳይ ሁሉ ያገባናል:: እንረዳ:: እንወቅ:: ደካማ ሕዝብ የገዢዎች ፈረስ ነውና!



ዳንኤል ተፈራ

# የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሁለት መልኮች ዘውድ እና ጎፈር

አንዳንዴ እንደዘበት የምንሰማቸው ነገሮች የሕይወታችን ገሃድ አካል ገልበው ያሳያሉ:: ቀልድ የሚመስሉን ነገሮች ድንገት የኑሯችን መራራ እውነት ይነግሩናል፤ በውስጣችን የሚልመዘመዘውን ሐቅ ያሳዩናል:: እናም መስማት ከፈለግን ተጨባጩን ጉዳያችንን አልባሌ ከሚመስሉ ሰዎች እንሰማለን::

እንሆ ለዚች አጭር ጽሑፍ መግቢያ ትሆነኝ ዘንድ የመረጥኳት ሐቅ ሦስተኛው የኅብረተሰብ ክፍል (ቁርሱን ከቀመሰ በኋላ ምሳውን ዘልሎ ከእራት ጋር ፈገግ ብሎ የሚኖረው ወይም በልቶ ማደርን እንደ ትልቅ ስኬት የሚቆጥረው አብዛኛው የኅብረተሰብ ክፍል ማለት ነው) የተገኘች ናት:: አንዲት ኑሮ ሲፈልግ በካልች ወይም በጥፊ ሲያላጋቸው የኖሩ የሚመስሉ እናት የዘመመ በር ተደግፈው ቁመዋል:: እንደመተከዝም እንደመታዘብም እያደረጋቸው ወጪ ወራጁን ይመለከታሉ:: በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ሌላ ወጣትነቷን ልሳ የጎልማሳነት በር ላይ የቆመች የምትመስል ሲያይዋት ገና ራሷ ‹‹ቀበሌ›› የምትመስል ደራቃ ቢጤ ሴት እኒያ ሴትዮ ጋር ስትደርስ እንደመቆም አለችና፡-

‹‹እርስዎ ግን ለምንድን ነው በተደጋጋሚ ስብሰባ ላይ የማይገኙት? እ?›› አለቻቸው::

‹‹አየ ልጄ አሁንማ አበል የለማ!›› ድህነት ያላሸነፋቸውን ውብ ጥርሶች የለበጣ ዓይነት ገለጥ አድርገው::

‹‹እ ምን አሉ? ምን?›› ቀበሌዋ እንደመውረግረግ ቃጣት:: እርሳቸው ግን ፈርጠም ብለው ከመጀመሪያው በበለጠ ቃላቱት ረገጥ አድርገው ደገሙላት::

> የአገርህ ፖለቲካ ነጻነት የማይሰጥህ ከሆነና በተሰፈረልህ መጠን ብቻ እንድትሰራ ካስገደደህ ማሽን ሆነሃል ማለት ነው:: በነጻነት አምራች የመሆን አቅምህ ተቀይዷል እንደማለት ነው

‹‹አበል የለም! አትሰሚም እንዴ! አበል በምርጫ ጊዜ ቀረ!›› አሉ የማይሰሙ ቃላትን እያጉተመተሙ ወደ ውስጥ ጥለዋት ዘለቁ::

ይህ ከላይ የገለጽኩት ነገር እውነት እንጅ ተረት ወይም ድርሰት አይደለም:: የሕወሓት/ኢሕአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝ ሁለት መልኮች በቀላል እውነት ሲገለጽ ማለት ነው:: ምርጫ ሲደርስ ያለው ኢሕአዴግና ከምርጫ በኋላ ያለው ኢሕአዴግ የተለያዩ ናቸው:: ከላይ ያነሳኧቸው እናት በብስጭት ሲናገሩ የነበረው በምርጫ ወቅት የነበረውን ሣምራዊውን ኢሕአዴግ ከምርጫ በኋላ በማጣታቸው ነው:: ይህ ለአብዛኛው ሕዝብ የሚሰወር ባይሆንም በድህነት ላይ መቆመር የሚፈልገው ፓርቲ እጅ የሚጠመዘዘው ድህነትን በመጠቀም ነው:: 40 ብር አንድ ሁለት ኪሎ ጨውና ስኳር ይገዛ ይሆናል:: ይህ በድህነት አረንቋ ውስጥ ላለ ሰው ቁም ነገር ሊሆን ይችላል::

ወደ ዋናው ርእሴ ጠምዘዝ ብዬ ስመለስ ማጠንጠኛዬ የሚሆነው ፖለቲካው ነው:: ወደድክም ጠላህም የተስተካከለ ፖለቲካ እስከሌለ ድረስ ሕይወትህ ሊስተካከል አይችልም:: ፖለቲካ በእያንዳንዱ ነገር ውስጥ ጥልቅ የማለት ባሕሪ አለው:: አምራች የመሆንና ያለመሆን አቅምህን የሚወስነው እንኳ ፖለቲካ ነው:: የአገርህ ፖለቲካ ነጻነት የማይሰጥህ ከሆነና በተሰፈረልህ መጠን ብቻ እንድትሰራ ካስገደደህ ማሽን ሆነሃል ማለት ነው:: በነጻነት አምራች የመሆን አቅምህ ተቀይዷል እንደማለት ነው:: ጠዋት በሻይ የምትበላት ዳቦ ሳትቀር መጠኗ የተወሰነው በፖለቲካ ነው:: ፖለቲካ ካልተስተካከለ የተሻለ ኢኮኖሚ አይኖርም፤ የተሻለ ኢኮኖሚ ከሌለ ደግሞ የተሻለ ዳቦ አትበላም፤ አራት ነጥብ:: እኔ ጣጣ የለኝም፤ ከዳንስና ከሳቅ በስተቀር ፖለቲካ አይመለከተኝም ብትል ብትል እንኳ ፖለቲካው ራሱ ይመለከተኛል ብሎ ወደ አንተ ይመጣል:: ለመደነስም የተረጋጋ ፖለቲካ ያስፈልጋልና:: ስለዚህ በአገራችን በተንሰራፋው የአንድ ፓርቲ ፖለቲካ ላይ ቸልተኛ አለመሆን የሚጠቅመው ራስን ነው ባይ ነኝ::

ከምክሩ ወደቁምነገሩ በድጋሚ ስመለስ በሕወሓት ፊታውራሪነት የሚመራው የአገራችን ፖለቲካ ባለሁለት መልክ ሆኖ እናገኘዋለን:: አንደኛው መልኩ ገድለህም፣ አስረህም፣ አሳደህም፣ አፍርሰህም፣ አስፈራርተህም ሥልጣንህን አስጠብቅ የሚለው ነው:: ይህን አስፈሪም አሳፋሪም የሆነውን መልክ ለባለፉት ሃያ አራት ዓመታት በደንብ የተመለከትነው ይመስለኛል::

ወደ ገፅ 10 ዞሯል

መንቶቼ የዕጽዋት (የባህል) መድኃኒት ማምረቻና መሸጫ
MENTOCHE HERBAL MEDICINE PRODUCTION CENTER



ይህ የዕጽዋት መድኃኒት ማዕከል ሲወርድ ሲዋረድ የነበረውን የአባቶች የባህል (እጽዋት) መድኃኒት ሕክምና በማሳደግ ፍቱንነታቸዉ ተረጋግጦ በከፊል በሳይንስና ቴክኖሎጅ በማስመዝገብና ከኢንቨስትመንት ፈቃድ በመውሰድ በማምረት ላይ ይገኛል። ለዉስጥ ችግር በሚወሰድ፣ በቆዳ ላይ ለሚወጣ በመቀባት ሲሆን ከኬሚካልም ሆነ ከባዕድ ነገሮች ነጻ የሆነ ነው። ከሚመረቱት ምርቶች በከፊል

በሚወሰድ
- ለኪንታሮት ፌስቱላ መድሀኒት በደም ዉስጥ ያለን አጥቦ የሚያወጣ ሲሆን ድርቀት፣ ወገብ ችግር፣ ጋዝና ወሲብ ችግርን ያድናል።
- ለነቀርሳ (ካንሰር) በሽታ ከደም ውስጥ አጥቦ የሚያወጣ በጭንቅላት፣ በአንገት፣ በጡትም ሆነ በአንጀት ላይ ያለዉን ያድናል።
- የደም ግፊት (ብዛት) እስከ መጨረሻዉ የሚያድን።
የኮሌስትሮል፣ የስብና የፕሮቲን ክምችትን ያቀልጣል፤ ስለሆንም ኮሌስትሮል ያጠፋል።
- ለነርቭ፣ ለሪህ፣ ለደም መወፈር (መርጋት) ለዲስክ መንሸራተት ያድናል።
- ለጉበት ሄፓታይተስ ሦስቱንም አይነት የጉበት በሽታ ያድናል።
- ለአእምሮ ጭንቀት ለሚጥል በሽታና ለሚያፈዘዉ ያድናል።
- ለቆዳ በሽታ አለርጅክም ሆነ ፈንገስ ሶራይሰስ ጭምር ያድናል።
- ኤድስን የሚያባብሱ ተዛማጅ በሽታዎችን በማከም የድካም ስሜትን፣ መክሳትንና የምግብ ፍላጎት መቀነስን እንዲጨምር ያደርጋል።
- በሆድ ዉስጥ ላለ በሽታ አሜባ፣ ታይፎይድ፣ ጃርዲያ፣ አስካሪስና ውሃ ወለድ በሽታዎችን ያድናል።
- ‹‹ሽንት ለሚያስቸግረውና ለስኳ በሽታ ፍቱን መድኃኒት አለን››

የሚቀባና በፊንጣጣ የሚገባ መድኃኒት
- ለኪንታሮት (ፊስቱላ) በሚቀባ ምንም አይነት ህመም የሌለዉ ሲሆን ሥራም የማያስፈታ ነዉ። ለቆየ የአባሳዘር ለዉስጥ ኪንታሮት በፊንጠጣ የሚገባ የዉስጥን የፈንገስ ክምችት የሚያወጣ ምንም አይነት የህመም ስሜት የሌለዉ ነዉ።
- ለቆዳ በሽታ ሁሉንም አይነት ያድናል
- ያለ እድሜ ለሚመጣ የወሲብ (የብልት መፍጠን) ችግር በመቀባት የሚያድን አብዛኛዉ ሕዝብ የኪንታሮት በሽታ መድሀኒት በተመጣጣኝ ዋጋ እንሸጣለን።

በተጨማሪም በመገናኛ ውልና ማስረጃ ፊት ለፊት ገነት ኮሜርሻል ሴንተር 2ኛ ፎቅ የመድኃኒት መሸጫና የመርጃ ማዕከል መክፈታችን ስናበስርዎ በደስታ ነው።
አድራሻ፡ አዲስ አበባ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ሃና ማርያም ከጤና ጣቢያው አለፍ ብሎ
0911 665321/ 0913 316790 / 0912 660886 / 011 4710024
ቁጥር 2፡ ሰሜን ሸዋ መሀል ሜዳ ወርልድ ቪዥን ፊት ለፊት